በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የመንገድ ፈንድ

## አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ

## የክትትል ኦዲት ሪፖርት

መስከረም 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ....................................................................................................i

ክፍል አንድ ....................................................................................................1

መግቢያ ....................................................................................................1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ ....................................................................................................2

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ....................................................................................................2

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ....................................................................................................2

ክፍል ሁለት ....................................................................................................3

በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣ ....................................................................................................3

ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፡ ....................................................................................................3

ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ .....7

በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ፡ ....................................................................................................8

ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ....................................................................................................9

ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን በተመለከተ፡ ....................................................................................................12

ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈዉ ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ እቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ ....................................................................................................14

የመንገድ ፈንድ ስትራቴጂክ እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ ....................................................................................................15

የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃ መኖሩን በተመለከተ፣ ....................................................................................................17

ጥገናውን ለማስፈጸም እና ወጥ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያዎች (Guide Lines and Procedure) ተዘጋጅቶ ለመንገድ ኤጀንሲዎች መሰራጨቱን በተመለከተ፣ ....................................................................................................20

የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 21

የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ 24

በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት መከናወኑን በተመለከተ ........ 27

በጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች የጥገና ታሪክ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ መኖሩን በተመለከተ ........ 28

የመንገድ ደህንነት ስራ ስለመሰራቱና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 30

ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት በተመለከተ ........ 31

ክፍል ሦስት ........ 34

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) ........ 34

3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ........ 34

3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው ........ 35

ክፍል አራት ........ 39

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) ........ 39

አባሪ -1- ........ 40

አባሪ 1.1 የ2005 ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበ ገቢ ........ 40

አባሪ 1.2፡ የ2006 በጀት አመት ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበገቢ ........ 41

አባሪ 1.3 የ2007 በጀት አመት ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበገቢ ........ 43

አባሪ 1.4 የ2008 በጀት አመት ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበ ገቢ ........ 44

አባሪ 1.5 የ2009 በጀት አመት፩/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበ ገቢ ........................................................ 46

አባሪ 2፡ ለመንገድ ኤጀንሲዎች 20 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፍያ እንዲጠቀሙ የተፈቀደበት ጊዜ ........................................................................................................................ 48

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የአገሪቷን የኢኮኖሚ እምርታ ለማፋጠንና የህዝቦቿን ኑሮ ለመለወጥ የሚያስችል ለጉዞ ምቹ የሆነና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ አውታር መኖር ለእድገቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በአገሪቷ በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የተገነቡ ብዙ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህ በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የተገነቡ መንገዶች ዘላቂ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ ተከታታይነት ያለው የመንገድ ጥገና እና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል፡፡ መንገድ በአግባቡ ከተገነባ ለጉዞ ምቹ ስለሚሆን ጊዜን ከማሳጠሩም በላይ ለተሽከርካሪውና ለተጓዦችም ደህንነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ይህ በመሆኑም መንገድ ከተሰራ በኋላ ለከፍተኛ ብልሽት ከመዳረጉ በፊት ጥገና ሊደረግለት ስለሚገባ ወጪውን ለመሸፈን ይረዳ ዘንድ የመንገድ ተጠቃሚዎችም ትኩረት በመስጠት የሚጠበቅብንን መወጣት ይኖርብናል፡፡

2. የአገሪቷን የመንገድ ጥገና እና የመንገድ ደህንነት ወጪዎች ለመሸፈን የመንገድ ፈንድ በአዋጅ ቁጥር 66/89 ተቋቁሞ ለፌደራል መንገዶች፣ለክልል ገጠር መንገዶች እና የፈንዱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለተመረጡ ወደ 60 ለሚሆኑ የከተማ አስተዳደሮች የመንገድ ጥገና በጀት እንዲሁም ለትራፊክ ደህንነት በየአመቱ ቀላል የማይባል በጀት እየመደበ ይገኛል፡፡

3. የመንገድ ፈንድ ለመንገድ ጥገና ወጪዎች የሚመድበው በጀት በስራ ላይ የሚውለው መንገዶችን ለመጠገንና ለመንከባከብ በአዋጅ ኃላፊነት በተሰጣቸው መንገድ ኤጀንሲዎች አማካይነት ሲሆን ይህ የመንገድ ፈንድ ሃብት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን መከታተልና መቆጣጠር ከመንገድ ፈንድ እና በጀቱ ከሚመደብላቸው የመንገድ ኤጀንሲዎች ይጠበቃል፡፡

4. ስለሆነም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ የአማካሪ ድርጅቶች እና የመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ እንዲሁም የመንግስት ሃብትና ንብረት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ለመከታተል ከሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል አካላት ጋር ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረጉን ስራ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

**የክትትል ኦዲቱ ዓላማ**

5. በመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደር ላይ የተሰራው ኦዲት ሪፖርት ላይ የተጠቀሱ ኦዲት ግኝቶች እና የተሰጡ ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ መኖሩን እንዲሁም ተገቢውን የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

**የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ**

6. የክትትል ኦዲቱ በዋናኛነት በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በናሙና በተመረጡ በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ጅማ ዲስትሪክት የመንገድ ጥገና ፅ/ቤት፣ ጅማ ማዘጋጃ ቤት ፣ ወሊሶ ማዘጋጃ ቤት፤ ሃዋሳ ማዘጋጃ ቤት፣ ደቡብ መንገዶች ዲስትሪክት እና ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤት የተከናወነ ሲሆን የክትትል ኦዲቱ በ2004 ዓ.ም በተደረገው የክዋኔ ኦዲት መሰረት ከ2005 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሰብ እና ኤጀንሲው ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት የተደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

7. የክትትል ኦዲቱ የተከናወነው ከ2005 በኃላ ያሉትን የቦርድ ቃለ ጉባኤዎች፤ለመንገድ ኤጀንሲዎች የተመደበ በጀት፣ እቅድ እና አፈፃፀም፤ በክብደት ላይ ከተመሰረተ የተሸከርካሪ ፍቃድ ማደሻ ላይ የወጣ አዋጅ፤ ፅ/ቤቱ ከፖስታ ቤት አገልግሎት ድርጅት ጋር ያደረገው ውል፣ በክብደት ላይ ከተመሰረተ የተሸከርካሪ ፍቃድ ማደሻ የተሰበሰቡ ገቢ ደረሰኞች፤ ከነዳጅ እና ዘይት ታሪፍ ከሚሰበሰቡ ገቢዎች ገቢ ደረሰኞች፤ ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሸከርካሪዎች የመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ ከሚሰበሰቡ ገቢዎች ገቢ ደረሰኞች፤ የቴክኒካል መስክ ምልከታ ሪፖርቶች እና የተሰጡ ግብረ መልሶች፤ የፋይናንሻል ኦዲት ሪፖርቶች እና የመሳሰሉት ማስረጃዎች በመከለስ፣ በፅ/ቤቱ እና በመስክ የሚገኙ የሚመለከታቸውን የስራ ሃላፊዎችን ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም በአካል ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ ተከናውኗል፡፡

**የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች**

8. የክትትል ኦዲቱን ለማከነወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## በክትትል ኦዲት ወቅት የተገኙ የኦዲት ግኝቶች፣

### ጽ/ቤቱ በአዋጁ መሰረት መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በሙሉ በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፡

9. ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ መሰብሰብ ያለበትን ገቢ በአዋጁ መሰረት በኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በኩል እየተሰበሰበ በወሩ መጨረሻ ገቢ መሆን ሲገባው ገቢ እንዳልተደረገ ፤ የመንገድ ጠቀሜታ ክፍያን ለመሰብሰብ ከኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር እና ከወጋገን ባንክ አክስዮን ማህበር ጋር የውል ስምምነት ያደረገ ቢሆንም ገቢው በውሉ መሰረት በወቅቱ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ እንዲሁም የኮሜት ትራንስፖርት አክስዮን ማህበር የሰበሰበው የውጭ ምንዛሪ በትክክለኛው የምንዛሪ ምጣኔ (rate) ገቢ ማድረጉን ለማረጋገጥ ኩፖኖቹ መቼ እንደተሸጡ የሚያሳይ መረጃ አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጦ ነበር፡፡

10. በዚህም ጽ/ቤቱ በአዋጁ እና በውሉ መሰረት ገቢዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ በእቅድ ሊሰራ፣ በአዋጁና እና በውሉ መሰረት ገቢዎችን በሙሉ በወቅቱ ሊሰበስብ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በዚሁ መሰረት የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

11. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የፈንዱ ገቢዎችን በሚመለከት በቀረበው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት እስከ ሰኔ 30/2004 ድረስ ያሉትን ክፍተቶች ፈትሾ ገቢዎቹ ሙሉ በሙሉ በወቅቱ የሚሰበሰብ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

12. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት እንደታየው

- ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ በኢትዮጲያ ነዳጅ ድርጀት በኩል እየተሰበሰበ የሚገኝ ቢሆንም ከ2005-2008 ዓ.ም ከ1 ወር እስከ 3 ወር ፤የ 2009 ዓ.ም እስከ 1 ወር ወደ ፅ/ቤቱ ገቢ መደረግ ካለበት ጊዜ መዘግየት የሚታይበት መሆኑን፣
- ከቅባትና ዘይት መሰብሰብ ያለበት ገቢ በነዳጅ ማደያ ድርጅቶች በኩል የሚሰበሰብ ሲሆን ከ2005-2009 ዓ.ም ከ1ወር እስከ 21 ወር ድረስ ወደ ፅ/ቤቱ

ገቢ መደረግ ከነበረበት ጊዜ የሚዘገይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 1 ተያይዟል)

- ከነዳጅና ቅባት ከአንድ ሊትር የሚሰበሰበው 10 ሳንቲም የገቢ መጠን ያልተሸሻለ መሆኑም ታይቷል፡፡
- ድንበር አቋርጠው ከሱዳን ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ የሚሰበሰብ ገቢ በወጋገን ባንክ በኩል የሚሰበሰብ ሲሆን ከ2005-2008 ከ1ወር እስከ 10 ወር ወደ ፅ/ቤቱ ገቢ መደረግ ከነበረበት ጊዜ የመዘግየት ሁኔታ ያለ ሲሆን
- 2009 ላይ መዘግየት ያልታየ እና የተስተካከለ መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

13. ድንበር አቋርጠው ከጅቡቲ ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ የሚሰበሰብ ገቢ በኮሜት ትራንስፖርት (የኢትዮጲያ ባህር ትራንዚት አክሲዮን ማህበር) በኩል የሚሰበሰብ ሲሆን

- ከ2005- 2007 ለፅ/ቤቱ የተጠቃለለ የገቢ ሪፖርት ቢቀርብም ተያይዞ ዝርዝር የሽያጭ ሪፖርት የማይቀርብ እና ከ2005-2006 የመቼ ወር የተሰበሰበ ገቢ እንዳስገቡ የማይገለፅ መሆኑ እንዲሁም
- በ2007 በአንድ አመት ውስጥ የተሰበሰበ ገቢ ከአንድ አመት ከ 6 ወር በኃላ ማለትም ከ5/9/2012- 2/8/2013 የተሰበሰበ በ13 feb 2015 ወደ ፅ/ቤቱ አካውንት ዘግይቶ እንዲገባ የተደረገ መሆኑ፣
- ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ የ2008 እና የ2009 በጀት አመት ተሰብሳቢ ሂሳብ ወደ ፅ/ቤቱ ምንም አይነት ገቢ ያላስገቡ መሆኑ ከጽ/ቤቱ ለሽያጭ ከተረከበው ኩፓን ውስጥ ቀሪ 25256 የኩፓን ብዛት የአንድ ኩፓን ዋጋ 15 ዶላር በመሆኑ በወቅቱ አማካኝ የምንዛሪ ተመን መሰረት (1 ዶላር በ 22.8874 ብር) 8,670,662.62 ብር ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ በተለያዩ ግለሰቦች አማካኝነት በቀን 26/11/2005 ዓ.ም እና 13/05/2006 ዓ.ም በድምሩ 2250 ኩፖን ወጪ በማድረግ ለሽያጭ የቀረበ ሲሆን በአንድ ኩፓን መሸጫ ዋጋ 15 ዶላር በመሆኑ የጠቅላላ የኩፓን ሽያጭ ዋጋ 33,750 ዶላር ወይም አሁን ባለው የዶላር ምንዛሪ ተመን መሰረት ብር 775,450.125 እስካሁን ድረስ ተሸጦ ገቢ መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለመቅረቡን፤

- በተጨማሪም ከኩፓን ቁጥር 040501 — 041500 ብዛት 1,000 ኩፓን ተሸጦ በሽያጭ ሪፖርት ላይ የቀረበ ቢሆንም ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ የተጠቀሱትን ቁጥር የያዙ ኩፖኖች ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ያልተረከበው መሆኑ፣
- ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ለመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ የሚሸጡ ኩፖኖች በወቅቱ ባለው የምንዛሬ ምጣኔ መሰረት መሸጣቸውን በተመለከተ ወጋገን ባንክ አ.ማ በሁመራ ቅርንጫፍ በኩል የሚሸጣቸውን ኩፖኖች በአንዱ ቀን የምንዛሬ መጠን አስልቶ ገቢ የሚያደርግ መሆኑ፡፡
- ኮሜት ትራንስፖርት አ.ማ ኩፖኖች በትክክለኛው ምንዛሬ መጠን መሸጣቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መቼ እንደተሸጡ የሚያሳይ ማስረጃ አለመያዙ

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

14. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃል መጠይቅ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በረቂቅ የክትትል ኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ የኢትዮጲያ ነዳጅ ድርጅት ነዳጅ በብድር ስለሚሸጥ ገንዘቡን አሰባስቦ ወደ ፅ/ቤቱ ለማስገባት እስከ አንድ ወር እንደሚዘገይ ባቀረበው ደብዳቤ መሰረት እያስገባ እና በ2009 ላይ ወሩ ባለቀ እስከ 15 ቀን ባለው እያስገባ መሆኑን የገለፁ ሲሆን የማደያ ድርጅቶቹን በተመለከተ ትንንሽ ገቢ የሚያስገቡ ማደያዎች በየ3 ወር የሚስገቡበት ሁኔታ መኖሩ እና ምክንያታቸውም በደብዳቤና በውስጥ ኦዲተሮች የተረጋገጠ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ወጋገን ባንክ ላይ የመሻሻል ሁኔታዎች መኖራቸው እና የኮሜት ትራንስፖርት የመዋቅር ለውጥ አድርጎ ወደ ኢትዮጲያ ባህር ትራንዚት አክሲዮን ማህበር በመግባቱ የኃላፊዎች መተካካት እና የፈራሚዎች መለዋወጥ ክፍተቶች እንዲፈጠሩ ማድረጋቸውን ከተሸጡ ኩፖኖች ገቢ ያልተደረገ 5 ሚሊየን ብር በወቅቱ ገቢ ባለመደረጉ ጅቡቲ ድረስ የፅ/ቤቱን ኦዲተሮች በመላክ ገንዘቡ በባንክ መኖሩ የተረጋገጠ መሆኑን እንዲሁም ጅቡቲ ላይ ሌላ የኢትዮጵያ ተቋም ባለመኖሩ ኮሜት ትራንስፖርትን እንደ ገቢ ሰብሳቢ ተወካይ ሊያቆዩት ማስገደዱን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኬላዎች ላይ ሳይከፍሉ ድንበር አቋርጠው በሚገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ በገቢዎችና ጉምሩክ በኩል ቁጥጥር እንዲደረግ ደብዳቤ የጻፉ መሆኑ ገልጸው፣ በኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ በኩል ገቢው በወቅቱ እንዲሰበሰብ ከተቋሙ ኃላፊዎች ጋር በፅሁፍም በአካልም የተነጋገሩ መሆኑን እንዲሁም አመራር ለሚሰጠው ሚኒስትር መ/ቤት ማለትም

በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር እና በትራንስፖርት ሚኒስቴር በኩል አመራር እንዲሰጥበት  የተደረገና ፅ/ቤቱም ጥብቅ ክትትል እያደረገ በመሆኑ በጅቡቲ ባንክ ያለውን ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ ተወካዮች በመመደብ በቅርብ ጊዜ ገቢ እንደሚያደርጉ ኮሜት ትራንስፖርት ኃላፊዎች ምላሽ ሰጥተዋል ያሉ ሲሆን አሁን ላይ ፅ/ቤቱም ገቢ ሊሰበስብ የሚችልበት የተሻለ አማራጭ በመፈለግ ላይ እንዳለም ገልፀዋል፡፡

15. የኩፖን ሽያጭ በወቅቱ ምንዛሬ ምጣኔ መሸጡን በተመለከተ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ በፅ/ቤቱ ፋይናንስ ሰራተኞች በኩል ወጋገን ባንክ ላይ ያሉትን ክፍተቶች ፈትሸው እንዲስተካከል እየሰሩበት መሆኑን፣ የኮሜትን በተመለከተ ግን የጅቡቲ ፍራንክ ምንዛሬ ምጣኔ ብዙ ጊዜ ተለዋዋጭ ባለመሆኑ ገቢውን ለማወቅ የተላከውን ኩፖን መጠን ካለው የቀን ስሌት ጋር በማየት የሚሰላ መሆኑን እንዲሁም ከነዳጅና ቅባት ከአንድ ሊትር የሚሰበሰበው 10 ሳንቲም የገቢ  መጠን ለማሻሻል ማክሮ ኢኮኖሚውን የሚነካ ስለሆነ በተፈለገው ጊዜ ዋጋ መጨመርና መቀነስ የማይቻል በመሆኑ ፅ/ቤቱ  ጥናት አስጠንቶ ለበላይ አካል ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት እንዳላገኘ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ተልኮ መሸጥ አለመሸጡ ስላልተረጋገጠው ኩፖን ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

16. የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ፅ/ቤቱ በነዳጅና ቅባት ላይ ከሚጣል ታሪፍ መሰብሰብ ያለበት ሁሉንም ገቢ በአዋጁ መሰረት በወቅቱ አለመሰብሰቡን እንዲሁም በኮሜት ትራንስፖርት ኢ.ማ በኩል ያለው ክፍተት ለረጅም ጊዜ ለመፍታት አለመቻሉን የኦዲት ቡድኑ አልተቀበለውም፡፡

17. ጽ/ቤቱ ከነዳጅና ቅባት እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የሚሰበስበውን ገቢ በአግባቡ እና በወቅቱ አለመሰብሰቡ ገቢው ለብክነት ብሎም ለምዝበራ እንዲጋለጥ በማድረግ የጥገና ሽፋን እንዳይጨምር ያደርጋል፡፡

## ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ

18. ከተፈቀደው ጭነት በላይ በመጫናቸው በሚጣል ቅጣት ለመንገድ ጽፈት ቤቱ መሰብሰብ የነበረበት ገቢ  ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ምንም ዓይነት ገቢ ተሰብስቦ እንዳልነበረ  በኦዲት ወቅት ታወቀ ነበር፡፡

19. በዚሁ መሰረት ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ

እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

20. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን የሚጣል የገንዘብ ቅጣትን በተመለከተ ያሉትን ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ላይ በመንገድ ጥገና የፋይናንስ ፍላጎት ጥናት ውስጥ ገቢው ወደ መንገድ ፈንድ ገቢ ሊሆን የሚችልበትን አኳሀን እና ሊጣል የሚገባው የቅጣት መጠን ያስጠና መሆኑን እና የጥናቱ ውጤት ከሀምሌ ወር 2004 ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንቅስቃሴ እንደሚያደርግ ገልፀዋል፡፡

21. ይሁን እንጂ የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከተደረገው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ በአዋጅ ላይ የሚዛን ጣቢያዎችን ማስተዳደርና ገቢ መሰብሰብ ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን መሆኑንና ፅ/ቤቱ ገቢን በሚመለከት መጣል ያለበትን ቅጣት አጥንቶ ለመንገዶች ባለስልጣን ያቀረበ ሲሆን እነሱም ለሚንስትሮች ምክር ቤት አቅርበው እስከ አሁን አለመፅደቁን ገልፀዋል፡፡

23. ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ ከክብደት በላይ የጫኑ አሽከርካሪዎች አስተማሪ ቅጣት እንዳያገኙ የመንገዶች ደህንነት እንዳይጠበቅ በማድረግ በክብደት ምክንያት መንገዱ የአገልግሎት ጊዜዉ እንዲያጥር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

**በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ መሰብሰቡን በተመለከተ፡**

24. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 66/89 መሰረት በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ያልሰበሰበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጠ ነበር፡፡

25. በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ሊሰበስብ እንደሚገባ የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበር ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

26. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በክብደት ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ ተሽከርካሪ ፍቃድ ማደሻ ክፍያን በተመለከተ ክፍያ እንዲወሰን ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት የቀረበ መሆኑን፣ በየዓመቱ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ በተደጋጋሚ ክትትል እየተደረገ እንደሆነና ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ተፈፃሚ እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

27. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በድርጊት መርሃ ግብሩ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ባይሆንም ሁለት አመት በመዘግየት በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ለማስፈፀም በየካቲት 2007 ዓ.ም ደንብ ቁጥር 340/2007 እንዲወጣ ተደርጎ ፅ/ቤቱ ከፖስታ ቤት አገልግሎት ድርጅት ጋር ውል በመዋዋል ከመስከረም 2008 ጀምሮ ገቢዎች በኢትዮጵያ ፓስታ አገልግሎት ድርጅት በኩል እየተሰበሰበ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

28. ይሁን እንጂ በገቢ አሰባሰቡ ሂደት ላይ

- በውሉ መሰረት ገቢዎቹ የሚቀጥለው ወር ከገባ እስከ 5 ባለው መሰብሰብ የነበረነት ቢሆንም ወቅቱን ጠብቆ የማይሰበሰብ መሆኑ በዚህም እስከ 6 ወር የመዘግየት ሁኔታ መኖሩ፤
- ገቢዎቹ ፅ/ቤቱ ባዘጋጀው ደረሰኞች የሚሰበሰቡ ቢሆንም የደረሰኞች ጥራዝ ተከታታይነት ቁጥር የሌላቸው መሆኑን፣ ከጥቅም ውጪ የሆኑ /ቮይድ የተደረጉ/ ደረሰኞች ዋና ቅጂው በደረሰኞች ውስጥ ተያይዞ አለመኖሩን፣

- ከሐምሌ1/2007- ሰኔ 30/2008 በስራ ላይ የዋለ ሰነድ ዝርዝር የያዘ የሂሳብ መግለጫ እና የተሰበሰበ ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ የተደረገበት የባንክ ስሊፕ ተያይዞ አለመቅረቡን በዚህም መቼ እና ምን ያህል ገንዘብ እንደተሰበሰበ ለማገናዘብ አለመቻሉን፣ በዚህም መሰረት ጽ/ቤቱ በ2008 በጀት ዓመት በክብደት ላይ በተመሰረተ ዓመታዊ የተሽከርካሪ ፋቃድ ማደሻ 240 ሚሊዮን ብር ለመሰብሰብ በዕቅድ የያዘ ቢሆንም 49 ፐርሰንት ብቻ ማለትም 118.34 ሚሊዮን ብር ብቻ የሰበሰበ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ስራው የተጀመረው ሐምሌ 2007 ላይ በመሆኑ የተሰበሰበውን ገቢ ጽ/ቤቱ ባሉት ውስን የፋይናንስ ሰራተኞች ለማጣራት ጥረት እያደረገ እና ስራው አመቱን ሙሉ የሚሰራ በመሆኑ ብዙ የስራ ጫና የተፈጠረባቸው በመሆኑ የውጭ ኦዲተሮች ቀጥረው ክፍተቶች እንዲለዩ የኦዲት ሥራ እየተሰሩ እንደሆነና ከውጭ ኦዲተሮቹ ሪፖርት በኃላ የታዩት ክፍተቶች ላይ የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30. የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በፅ/ቤቱ የውስጥ ኦዲተሮች በተሰራው ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች መሰረት የመፍትሄ እርምጃዎች መውሰድ ስላልጀመሩ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

31. ከክብደት በላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ በአግባቡ እና በወቅቱ እንዲሰበሰብ አለመደረጉ ገንዘቡ ለብክነት እንዲጋለጥ ከማደረጉም በላይ ሥራዎች እንዲዘገዩ እና ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

32. ከመንገድ ፈንዱ የተወሰደ ገንዘብ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እንዲያስችል አማካሪ ድርጅት ቢቀጠርም የተቀጠሩ አማካሪ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን በሚገባ ስለመወጣታቸው ለማረጋገጥ በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖሩና እንዲሁም የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የፈንዱን አጠቃቀም በተመለከተ በመንገድ ኤጀንሲዎች የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ በበቂ ደረጃ አለማከናወኑን፣ የውስጥ ኦዲቱም በመንገድ ኤጀንሲዎች በመገኘት የሂሣብ ምርመራ ሥራ አለመሠራቱና በመስክ ተከታታይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር

ሥራ አለማከናወኑ፣ የተቀጠሩ አማካሪ ድርጅቶች የክትትልና የቁጥጥር ሥራውን በአግባቡ እየሠሩ አለመሆኑ፣ በተባሉበት ቦታ የማይገኙ እና ክትትልም የማያደርጉ መሆኑንና ፣ ያላቸው የሰው ኃይል ከሚሠራው ሥራ ጋር ተመጣጣኝ ስላልሆነ የቁጥጥሩ ሥራ የሚፈለገውን ያህል እንዳልሆነ፣ የማማከር ሥራቸውን በተገቢው መንገድ ለማከናወናቸው የቅርብ ክትትል እና ቁጥጥር ሳይደረግ የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ የሚከፈል መሆኑን እንዲሁም የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ሙያው የሚጠይቀው የቴክኒክ ባለሙያዎች የሌለው በመሆኑ ተገቢው የፕሮጀክቶች ብቃት ምዘና በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑና የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በእቅዱ ላይ ቢታይም የፋይናሻልና ቴክኒካል ኦዲት ያላደረገ መሆኑ የኦዲቱ ወቅት ተገኝቶ ነበር፡፡

33. ጽ/ቤቱ ለመንገድ ለጥገና እና ደህንነት ፈንድ ሲሰጥ ገንዘቡ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እንዲያደርግም የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

34. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት በተመለከተ ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ነገር ግን ክፍተቶች በኦዲቱ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ተፈትሾ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

35. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ፅ/ቤቱ ከ2005 ጀምሮ የቴክኒካል ኦዲት ክፍል ለብቻው ማደራጀቱ ታውቋል፡፡ ነገር ግን

    - በፈንዱ ገንዘብ ለተሰራው ስራ ተገቢውን ክፍያ መፈጸሙን በተመለከተ በ2006 በጀት አመት በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን ስር በሎቄ - ሻመና እና በሀላባ ደንቦያ መንገድ መስመር ላይ በአንድ የጥገና መንገድ ላይ በሁለት የተለያዩ የስራ መደቦች ሁለት ጊዜ ክፍያ እንደሚፈጸም እንዲሁም በሀዋሳ መዘጋጃ ቤት አማካሪው ድርጅት የተሰራውን ስራ

ሳይለካ  የነዳጅ ወጪያቸውን ወደ መንገድ ፈንድ ነጠላ ዋጋ ስሌት (የአንድ ኪሎ ሜትር ጠቅላላ ዋጋ) በመቀየር የሚሰራ መሆኑ፤

- በ2008 በጀት አመት በአማራ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን አማካሪ ድርጅቱ የተቀጠረ ቢሆንም አማካሪው ድርጅቱ በክልል ቢሮ እንደሌለው ክፍያ እንዲያጸድቅ ሲጠየቅ ብቻ እንደሚያፀድቅ እና ስራው ላይ ምንም አይነት አስተዋጽዎ እንደሌለው፣
- በ 2006 በጀት አመት በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን የጥገና ስራዎች ተሰርተው ሳይጠናቀቁ እንዳለቁ ተደርጎ ክፍያ የሚጠየቅባቸው እና አማካሪውም የክፍያ ጥያቄ የሚያፀድቅበት ሁኔታ መኖሩ፣ በምዕራብ ሸዋ የጥገና ዲስትሪክት የጉደር- ሸነን የጥገና መስመር 57 ኪ.ሜ የሚሸፍን ቢሆንም የጥገና መስመሩ ስራ ሳይጠናቀቅ እና ገና በመሰራት ላይ እያለ አማካሪው ድርጅት ስራው እንደተጠናቀቀ ተደርጎ ሙሉ ክፍያውን ማጽደቁን ከተከለሱ ማስረጃዎች መገኘታቸው፣
- በወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በክልሉ መንገድ ባለስልጣን የተቀጠረላቸው አማካሪ ድርጅቱ በከተማው ጽ/ቤት ያልከፈተና ተቀምጦ የማይሰራ ሲሆን የሰው ሀይሉም አነስተኛ  እንደሆነና ለስራ ሲፈለግ በስልክ ተጠርቶ እንደሚመጣና ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የሚጠቀሙበትን ግብዓት ስለትክክለኘነቱ የላብራቶሪ ፍተሻ/ቴስት እንደማያደርግና የክፍያ ሰርተፍኬት እየመጣ እንደሚያጸድቅ መግለፃቸው፣
- ፈንዱ ለታቀደለት ፕሮጀክት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የተቀጠሩት አማካሪ ድርጅቶች ካላቸው የሰው ሀይል አንጻር አንድ ተቆጣጣሪ መሀንዲስ (work inspector) በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙትን ሁለትና ከዛ በላይ ዲስትሪክት እና ከተማ ማዘጋጃ ቤቶችን እንዲቆጣጠር መደረጉ፣ ለዚህም ማሳያ  በደቡብ ክልል 11 ዲስትሪክት ጥገና ጽ/ቤት እና 11 ከተማ መዘጋጃ ቤቶችን በዳቤክ አማካሪ ድርጅት የተያዘና ለአማካሪውም 2,023,488.25 ብር የተመደበለት ሲሆን በ1 ዋና መሀንዲስና በ7 የስራ ተቆጣጣሪ ማለትም በአማካኝ 1-3 በተለያዩ ቦታዎችን እንዲሰራ መደረጉ ፤በአማራ ክልል በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ 4 ዲስትሪክት እና ለ14 ከተማ መዘጋጃ ቤቶችን በቤስት አማካሪ ድርጅት የተያዘና ለአማካሪውም 3,851,350 ብር የተመደበለት ሲሆን  በ2 ዋና መሀንዲስና በ8 የስራ ተቆጣጣሪ ማለትም በአማካኝ 1-2 ቦታዎችን እንዲሰራ መደረጉ

ይህ ደግሞ ስራዎች ከተሰሩ በኃላ አማካሪው ለመመልከት ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ስራዎችን በቦታው ተገኝቶ እንዲደግፍና ሙያዊ እገዛ በማድረግ ፈንዱ ለታቀደለት ዓላማ እንዲውል አለማስቻሉ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ የተቻለ በመሆኑ እንደ ክፍተት የተወሰዱ ነጥቦች ናቸው::

36. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ የአማካሪዎችን የሰው ሃይል በሚመለከት ከሚመደብላቸው በጀት አኳያ 1 አማካሪ 3 ወይም 4 ቦታዎች የሚሸፍኑ በመሆኑ ወሩን በሙሉ ላይገኙ እንደሚችሉ ፣ ዋና በጀት በሚመደብላቸው የገጠር መንገዶች ላይ ግን ወሩን በሙሉ እየሰሩ እንደሚገኙ፣ ሳይገኙም ከቀሩ እርምጃ እየተወሰደባቸው እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

37. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ከላይ በክትትል ኦዲቱ ግኝት እንደታየው አማካሪዎች ወሩን በሙሉ ለመከታተል ውል የገቡ በመሆኑ እንዲሁም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ብሮች የተመደበላቸው አማካሪ ድርጅቶችን ትንሽ በጀት የሚመደብላቸው ስለሆነ የሚለውን አስተያየት ለመቀበል የኦዲት ቡድኑ ይቸገራል፡፡

አማካሪዎች ያላቸው የሰው ሃይል ከሚጠበቅባቸው ስራ አንፃር አነስተኛ መሆኑ እንዲሁም ያልተሰሩ ስራዎች እንደተሰሩ ሆነው ክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ተሰጥቷቸው ክፍያ የሚፈፀም መሆኑ በፅ/ቤቱ ለጥገና የተመደበው ፈንድ በትክክል ስራ ላይ እንዳይውል ያደርገዋል፡፡

## ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን በተመለከተ፡

38. ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን ማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት የመንገድ ኤጀንሲዎች የፋይናንሻል እና የፊዚካል እቅዳቸውን ሲያቀርቡ ከሚመደበው በጀት ጋር የሚጣጣም ለመሆኑ በባለሙያ አለመታየቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

39. ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረብ እንዳለበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

40. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን እንዲሁም በመንገድ ኤጀንሲዎች የሚቀርበው ዕቅድ ተዓማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ ከመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም ጀምሮ የዕቅድ ዝግጅት ለማሻሻል የተጀመረው ተግባር እንደሚጠናቀቅና ከዚህ በፊት የታዩ ድክመቶችን በማረም ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የተሻለ ስራ እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

41. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ፅ/ቤቱ በሦስት አይነት አማራጮች ማለትም 1ኛ በመንገድ ሁኔታ ጥናት መሰረት የመደበኛና ወቅታዊ የመንገድ ጥገና የሚያስፈልጋቸው መንገዶች የበጀት ገደብ ሳይኖር የፊዚካል እና የፋይናንሻል እቅድ 2ኛ በባለፈው አመት ከተመደበው በጀት ላይ 10 በመቶ በመጨመር እና 3ኛ በባለፈው አመት ከተመደበው በጀት ላይ 30 በመቶ በመጨመር ጥገና ከሚያስፈልጋቸው መንገዶች ውስጥ ወሳኝ የሆኑትን በመምረጥ የፊዚካልና የፋይናንሻል እቅድ እንዲያዘጋጁ የሚያሳስብ ደብዳቤ እና የእቅድ አቀራረብ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚልክ መሆኑ እና የመንገድ ኤጀንሲዎች የፋናንሻልና የፊዚካል እቅዳቸውን ለፅ/ቤቱ በሚልኩበት ጊዜ በተላከላቸው መስፈርት መሰረት ማቀዳቸውን በቴክኒካል እና ዕቅድ ግምገማ እና ክትትል ባለሙያዎች እየተገመገመ እቅዳቸው የሚፀድቅ ቢሆንም የእቅድ ግምገማዎች ዘግይተው የሚከናወኑ መሆኑ ለዚህም ማሳያ ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን የ2007 በጀት አመት ዕቅድን በ19/02/07፣ የ2009 በጀት አመትን በ06/01/09፤ የጅማ ማዘጋጃ ቤት የ2009 በጀት አመት በ09/01/09 እቅዳቸው መገምገሙን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ይህ የሆነበት ምክንያት የመንገድ ጥገና እንደ ሌሎች ስራዎች ክረምት ላይ የሚሰራ/ የሚጠገን ባለመሆኑ እንዲሁም የፅ/ቤቱ ሰራተኞች ውስን በመሆናቸው ሌሎች የሚቀድሙ ስራዎችን አስቀድመው ግብረ መልሶቹ ከዛ በኃላ እንደሚሰጡ በዚህም ምንም ተፅእኖ እንዳላሳደረባቸው ገልጸዋል፡፡

43. ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በፅ/ቤቱ የዜጎች ቻርተር ላይ በተቀመጠው መሰረት የእቅድ ግምገማ ግብረ መልስ የሚሰጥበት ጊዜ እስከ 3 ቀን ባለው የሚል መሆኑና እቅዶቻቸው በወቅቱ ተገምግመው የተስተካከለ እቅድ ከበጀት አመቱ በፊት እንዳያዘጋጁ ስለሚያደርጋቸው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

44. የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ ግምገማዎች የበጀት አመቱ ከመጀመሩ በፊት ግብረመልስ የማይሰጥባቸው በመሆኑ ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚለቀቀው በጀት እንዲዘገይና ስራዎች እቅዳቸውን ተከትለው በበጀት አመቱ እንዳይጠናቀቁ ያደርጋል፡፡

## ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈዉ ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ እቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን በተመለከተ

45. ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚፈቀደው በጀት በወቅቱ ባለመጽደቁ፣ የበጀት ዓመቱ ከመግባቱ አንድ ወር አስቀድሞ የጸደቀው አመታዊ እቅድ እና በጀት ለመንገድ ኤጀንሲዎች በወቅቱ እንዲደርስ ባለመደረጉ፣ በናሙና በተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲሁም ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት በመገኘት በተደረገው ማጣራት የመንገድ ኤጀንሲዎች በተፈቀደው ዓመታዊ እቅድ መሠረት ሥራቸውን ለማከናወን ያለመቻላቸውና በመንገድ ኤጀንሲዎች አፈጻጸም ላይ አልፎ አልፎ አሉታዊ ተጽኖ ማሳደሩም በኦዲቱ ወቅት ታውቆ ነበር፡፡

46. ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ እቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋል እንዳለበት የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

47. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱም በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በፀደቀው አመታዊ እቅድ መሰረት ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ለመንገድ ኤጀንሲዎች ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የማስፈጸም አቅም የመገንባት ስራዎች እንደሚሰሩ በድርጊት መርሃ ግብራቸው ላይ ገልፀዋል፡፡

48. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በመንገድ ፅ/ቤት ቦርድ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ፈንድ የፀደቀው የ2007 በጀት በነሀሴ 22 ቀን፣ 2006 ዓ.ም ፤የ2008 በጀት በመስከረም 22 ቀን 2008 ዓ.ም እንዲሁም የ2009 በጀት ደግሞ በመስከረም 14 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ መዘግየት የሚታይበት ከመሆኑም በተጨማሪ ለመንገድ ኤጀንሲዎች 20 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፍያ እንዲጠቀሙ የሚፈቀድላቸው ከ1ኛ-4ኛሩብ አመት የሚዘገይ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡)

49. በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች

- ጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በጀቱ በወቅቱ ጸድቆ እንደማይለቀቅና ለምሳሌ የ2009 በጀት ዓመት በጀቱ የተለቀቀው ጥር ወር ላይ መሆኑ፤
- በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ጅማ ዲስትሪክት የ2009 በጀት ዓመት በጀቱ ጸድቆ የደረሰው ጥቅምት ወር ላይ 1ኛ ሩብ ዓመት ካለቀ በኃላ በመሆኑ ስራዎቹ በግዜ እንዳይጠናቀቁ ተፅእኖ እየፈጠረ መሆኑ፣ ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የ2009 በጀት ዓመት በጀቱ ጸድቆ የተለቀቀው ሚያዚያ ወር ላይ መሆኑ ታውቋል፡፡ የታየ መሆኑ ታይቷል፡፡

50. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቃለ መጠይቅ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ አዲሱ በጀት ከመልቀቃቸው በፊት የመንገድ ኤጀንሲዎች የቀድሞ በጀት እስከ ሐምሌ 30 የችሮታ ጊዜ ድረስ ስራዎች ካከናወኑ በኃላ በባንክ ያለ ቀሪ ሂሳብ ስቴትመንት፣ የበጀት አመቱ የፋይናንስና የፊዚካል አፈፃፀም ሪፖርት፣ በመንገድ ፈንድ ቼክ ሊስት መሰረት በበጀታቸው ልክ የተስተካከለ እቅድ ማቅረብ እንደሚጠበቅባቸው እነዚህን ያሟሉ የመንገድ ኤጀንሲዎች ከነሐሴ እስከ መስከረም ባለው በጀት የሚለቀቅላቸው መሆኑን፣ ከሁለተኛ ሩብ አመት በላይ ይዘገይባቸዋል የተባሉት ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርት ያላሟሉ የመንገድ ኤጀንሲዎች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

51. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ አስተያየታቸውን የሚያስደግፍ የተሟላ ማስረጃ ባለማቅረባቸውና በጀቱም ዘግይቶ የሚጸድቅ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

52. ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በወቅቱ የማይጸድቅ በመሆኑ በዓመታዊ እቅድ መሰረት ስራው በጥራት እንዳይሰራና በጀቱ ተመላሽ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

## የመንገድ ፈንድ ስትራቴጂክ እቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ

53. በጽ/ቤቱ ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመት የተዘጋጀው የስትራቴጂክ እቅድ ሲታይ በእቅዱ ዓመት መጨረሻ (በ2002 ዓ.ም.) የመንገዶችን ጥራት ደረጃ በማሻሻል የአስፋልት፣ የጠጠር እና የገጠር መንገዶች ሁኔታ እንደቅደም ተከተላቸው አሁን ከሚገኙበት 43%፣ 31% እና 30% ወደ 80%፣ 60% እና 50% ለማሳደግ በእቅዱ የተያዘ ቢሆንም ይህ እቅድ የጽ/ቤቱ ድርሻ በግልጽ ካለማሳየቱም በላይ አፈጻጸሙን ለመገምገም ያለመቻሉን ፤የመንገድ ጥገና አማካይ የኪ.ሜ ወጪን መቀነስ

የሚያስችል ስልት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቆ ነበር፡፡ በተጨማሪም በጽ/ቤቱ ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመት የተዘጋጀው የስትራቴጂክ እቅድ ሲታይ፣ የመንገድ ጥገና የኪሎ ሜትር ወጪ በአስፋልት ጠጠር እና የገጠር መንገድ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው 20 ሺህ 15 ሺህ እና 5 ሺህ የሚገመተውን የመደበኛ ጥገና ወጪ በ2002 መጨረሻ ወደ 5 ሺህ፣ 5 ሺህ እና 3 ሺህ ዝቅ እንዲል የመንገድ ጥገና ሥራን በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሥራት የተያዘው እቅድ ተግባራዊ አለመደረጉ ተረጋግጦ ነበር፡፡

54. በዚሁ መሰረት በጽ/ቤቱ የሚዘጋጀው የስትራቴጂክ እቅድ ከመንገድ ዘርፍ አጠቃላይ የልማት ፕሮግራም በመነሳት በጽ/ቤት ደረጃ ሊሠራ የሚቻለውን በመለየትና በተያዘው እቅድ መሠረት በመፈጸም የጽ/ቤቱ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ሊካተት እንደሚገባ፣ እንዲሁም የመንገድ ጥገና የኪሎ ሜትር ወጪ በስትራቴጂክ እቅድ ከመዘጋጀቱ በፊት በቂ የሆነ ጥናት ላይ የመሠረተና ሊተገበር በሚችል መልኩ እንዲዘጋጅ የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

55. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱም በላከው በድርጊት መርሃ ግብር ላይ በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት የመንገድ ፈንድ ስትራቴጂክ እቅድ እና የመንገድ ጥገና የኪሎ ሜትር ወጪ በቂ የሆነ ጥናት ላይ ተሞርኩዞ እንዲተገበር ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ለማድረግ በሚዘጋጀው እስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

56. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በፅ/ቤቱ ከ2008-2012 ባለው ጊዜ ለመፈጸም የስትራቴጂክ እቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ የመንገዶችን ጥራት ደረጃ ለማሻሻል የሚል ያልተያዘና በተመረጡ የመስክ ናሙናዎች በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ጅማ የመንገድ ጥገና ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና ጅማ ማዘጋጃ ቤት፣ ወሊሶ ማዘጋጃ ቤት፣ ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤት፣ በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን እና አዋሳ ማዘጋጃ ቤት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆኑ ታይቷል፡፡

57. የነጠላ ዋጋን በሚመለከት የነጠላ ዋጋ በኪሎ ሜትር ሳይሆን በሚሰሩት ስራዎች ዝርዝር በሜትር ኪዩብ/ ስኬር እየተለኩ የሚያወጡት ወጪ በ2005 እና 2009 የተጠና ጥናት ቢኖርም በተጠናው የነጠላ ዋጋ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለፅ/ቤቱ በቀረበው ቃለ መጠይቅ ተረጋግጧል፡፡

58. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ የመንገዶችን ጥገና ጥራት ደረጃን በተመለከተ የመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት የመንገድ ጥገና ፋይናንስ ማድረግ ስልጣን ያለው በመሆኑ እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ያወጣው ስታንዳርድ የመንገድ ሁኔታ የሚገልፅ በመሆኑ በዛው መሰረት እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ፣ የተከለሰው የነጠላ ዋጋን በሚመለከት ስራው በመንገድ ኤጀንሲዎች የሰው ሃይል የሚሰራ ከሆነ የተጠናው ነጠላ ዋጋ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ከሚመደበው በጀት ጋር የማይጣጣም ሁለት እጥፍ ጭማሪ የሚስፈልገው በመሆኑ ተግባራዊ አለመደረጉን፣ ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኛው ስራዎች የሚሰሩት ገበያ መር በሆነ የጨረታ ስርአት እንደመሆኑ አብዛኛው የመንገዶች ጥገና በገበያው ዋጋ የሚወሰን በመሆኑ የነጠላ ዋጋ ትርጉም እንደሌለው ሆኖም ግን በተወሰነ በራስ ሃይል ለሚሰሩ የመንገድ ኤጀንሲዎች የነጠላ ዋጋ በተለያየ ጊዜ እየተሻሻለ በፀደቀው የነጠላ ዋጋ መነሻነት የበጀት አቅምን በማገናዘብ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

59. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በመስክ በናሙና በታዩ በራሳቸው ሃይል መንገዶችን የሚጠግኑ የመንገድ ኤጀንሲዎች የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ባወጣው ስታንዳርድ የማይጠቀሙ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

60. የሚጠገኑ መንገዶች የጥራት ደረጃ ከማሻሻል አንፃር ፅ/ቤቱ ያስቀመጠው ግብ ባለመኖሩ የመንገዶች የጥገና ጥራት በየወቅቱ እንዳይሻሻል የሚያደርግ ሲሆን የሚሰሩት ስራዎች ዝርዝር የሚያወጡት ወጪ የተጠና ጥናት መኖሩ ስራዎች ያላቸው የነጠላ ዋጋን እንዲታወቅና በዛም መሰረት እንዲተገበሩ ለማድረግ የሚረዳ ቢሆንም የተጠኑ ጥናቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ አለመደረጉ የሚሰሩ ስራዎች በትንሽ ወጪ ለመስራት በሚደረግ ጥረት የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዳይሰሩ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

### የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃ መኖሩን በተመለከተ፣

61. የመንገድ ጥገና ደረጃ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በኩል እንደተዘጋጀ ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም፣ በኦዲቱ በመስክ ጉብኝት ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት መሠረታዊ የመንገድ ጥገና ደረጃን ተከትለው የመንገድ ጥገና ሥራዎች ወጥ (standardize) በማድረግ እየተጠገኑ እንዳልሆነ ፣ በናሙና ከተመረጡ የመንገድ ኤጀንሲዎች የመንገድ ጥገና ሂደት መሰረታዊ የጥገና ደረጃ ኖሮት እንደማይከናወን

ለመረዳት የተቻለና በጽ/ቤቱም በዚህ ዙሪያ የተከናወነ ተግባር አለመኖሩ፤ እንዲሁም ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ጥገናው የሚከናወንበት ደረጃ ባለመኖሩና፣ ለጥገና የሚጠቀሙበት ግብዓት እና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ ተወስኖ ተግባራዊ ባለመደረጉ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቶችም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ሳያደርጉ ተሰራ ተብሎ የቀረበውን የክፍያ ሰርተፊኬት ያለገደብ የሚያረጋግጡ በመሆኑ በጊዜ እና በዋጋ ከእቅድ በላይ የሆኑት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መኖራቸው እንደ ግኝት የተወሰዱ ነጥቦች ነበሩ፡፡

62. የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃ፣ ለጥገና መጠቀም የሚገባቸው ጥሬ እቃ እና ፕሮጀክቱ የሚወስደውን ጊዜ በተመለከተ ግልጽ በሆነ መልኩ በማስቀመጥ ወጥ የሆነ የጥገና ደረጃ ሊኖርና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

63. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱም የማሻሻያ ሃሳቡን በተመለከተ የመንገድ ጥገና ሂደት መሰረታዊ የጥገና ደረጃ መኖሩን በተመለከተ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road mentenance, design and standared ያለ በመሆኑ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ እንዲደርሳቸው እንደሚደረግና ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የመንገድ ኤጀንሲዎቹ በእነዚህ መመሪያዎች መሰረት መስራታቸውን እንደሚያረጋግጡ የድርጊት መርሃ ግብራቸው ላይ ገልፀዋል፡፡

64. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲት ወቅት፡

- በ2007 በጀት ዓመት በድሬዳዋ ከተማ በመሰራት ላይ ካሉት በ 02 መስቀለኛ አካባቢ በ 7 ጥገና መስመሮች ላይ እና በአሸዋ የገበያ ቦታ አካባቢ እንዲሁም በሱማሌ ገጠር መንገድ ባለስልጣን በኩል በ2006 በጀት ዓመት በወቅታዊ መንገዶች ጥገና ከተጠገኑት ውስጥ ከጂጂጋ - ቱሊጉሌት ያለው 30 ኪ.ሜ የኢትጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road mentenance, design and standared መሰረት እየተሰራ እንዳልሆነ፣
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ጅማ ዲስትሪክት ለማቴሪያልና ለስራው ጥራት ቅድሚያ ሰጥቶ በውለታው ሰነዱ መሰረት በሳይቱ ላይ ጊዜያዊ ላብራቶሪ ግንባታና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማሟላት የነበረበት ቢሆንም በሳይቱ ላይ የላብራቶሪ ግንባታ አለመካሄዱ በዚህም ጥቅም ላይ የዋለው

ማቴሪያል ለ(surface course) የማይሆን በ(visual inspection low CBR,highly plastic) የሆነ ደካማ ማቴሪያል በመሆኑ እና መንገዱ መጀመሪያ ከነበረው ማቴሪያል ጋር ሲነፃፀር ደካማ ጥራት ያለው በመሆኑ የመንገዱን ደረጃና ጥራት ዝቅ የሚያደርግ እንዲሁም አካባቢው በጣም ዝናባማ በመሆኑ መንገዱ ተጠግኖ የሚጠበቀውን አገልግሎት መስጠት እንደማይችል በተጨማሪም ከመቱ- አልጌ በሚወስደው ጥገና መስመር ተመሳሳይ የማቴሪያል የጥራት ችግር መኖሩ፣

- የጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የውስጥ ለውስጥ የጥገና መንገዶች የጥራት መጠናቸው ዝቅተኛ የሚባል መሆኑና የሚጠቀሙበት ማቴሪያል (engineer-ing characteristics) ሲታይ (high plasticity expensive decomposed trachayet)የሚባለው ሲሆን ይህ የአፈር አወቃቀር ውሃ በሚያገኝ ጊዜ የማበጥና ሸክም የመያዝ አቅሙን ጨርሶ ሚጠፋበት ባህሪ ስላለው የመንገዱን (durability, surviciablity and load bearing capacity) አለመኖሩ

ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማየት ተችሏል፡፡

65. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃል መጠይቅ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ በኮንትራት ለሚጠገኑ መንገዶች ለመንገድ ጥገናው መጠቀም የሚገባቸው ጥሬ እቃዎች ጠብቀው በውሉ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው በመሃንዲሶች እየተረጋገጠ ክፍያ እየተፈፀመ እንደሚገኝ እንዲሁም የመንገድ ኤጀንሲዎች በራሳቸው አቅም ለሚጠግኗቸው መንገዶች ተሸሽለው በተጠናው ነጠላ ዋጋ ለመስራት በጀታቸው የማይፈቅድ በመሆኑ የማቴሪያሉ፣ የባለሙያው ፣ የኮንስትራክሽኑ እና የማሽኑ ጥራት ለሚጠገነው መንገድ ጥራት መጓደል መንስኤ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

66. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ በፅ/ቤቱ በሚያከናውናቸው የመስክ ጉብኝት በታዩ ሪፖርቶች ላይ በተገኙ ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ስለመወሰዳቸው ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ አስተያየታቸውን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

67. በመንገድ ኤጀንሲዎች ስር ያሉ መንገዶች የመንገድ የጥገና ሂደት መሠረታዊ የጥገና ደረጃን ተከትለለው ለጥገና መጠቀም የሚገባቸው ጥሬ እቃ ባለመጠቀማቸው መንገዶቹ በሚፈለግባቸው ጥራት እንዳይጠገኑ እና ተገቢውን

አገልግሎት እንዳይሰጡ ብሎም አገልግሎት ይሰጣሉ ተብሎ ከተያዘላቸው ጊዜ ቀድመው እንዲበላሹ ምክንያት ይሆናሉ፡፡

**ጥገናውን ለማስፈጸም እና ወጥ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያዎች (Guide Lines and Procedure) ተዘጋጅቶ ለመንገድ ኤጀንሲዎች መሰራጨቱን በተመለከተ፣**

68. በናሙና ከተመረጡ አብዛኞቹ የመንገድ ኤጀንሲዎች የጥገና ደረጃን ወጥ ከማድረግ አንጻር በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት መመሪያና ስለአፈጻጸሙ ሥርዓት (Guide Lines and Procedures) ያልደረሳቸው መሆኑ አንዳንድ የመንገድ ኤጀንሲዎችም በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የተዘጋጀ መመሪያ የደረሳቸው ቢሆንም በጽ/ቤቱ የሚመደብላቸው የገንዘብ መጠን አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ መመሪያውን ተግባራዊ እንዳላደረጉ የሚሉት የተገኙ ግኝቶች ነበሩ፡፡

69. የመንገድ ጥገና ጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል GUIDE LINE & PROCEDURE ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ፅ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

70. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል። ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የመንገድ ጥገና የጥራት ደረጃ ለማረጋገጥ GUIDE LINE & PROCEDURE ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚለውን በተመለከተ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road maintenance, design and standard ያለ በመሆኑ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ እንዲደርሳቸው እንደሚደረግና ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የመንገድ ኤጀንሲዎቹ በእነዚህ መመሪያዎች መሰረት መስራታቸቸውን እንደሚያረጋግጡ ገልፀዋል፡፡

71. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በመስክ የታዩ ወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ ጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ፣ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ጅማ ዲስትሪክት መንገድ ጥገና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road maintenance, design and standared መመሪያ ያልደረሳቸውና በዛም መሰረት ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆኑ ታይቷል፡፡

72. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ መመሪያው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የወጣ በመሆኑ ለክልል መንገድ ኤጀንሲዎች ማሰራጨት በዋነኝነት የባለስልጣን መ/ቤቱ መሆኑንና ፅ/ቤቱ በበኩሉ በተለያዩ ጊዜያት የመመሪያ ስርጭት የሚያደርግ ቢሆንም በመንገድ ኤጀንሲዎች የሰው ሃይል ፍልሰት ስላለ የነበረው አመራር ለሚቀጥለው ያለማስተላለፍ ችግር እንዳለ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን እና መንገድ ፈንድ ፅ/ቤት በጋራ ወርክ ሾፖች ላይ ኤጀንሲዎች መመሪያውን እንዲያገኙ እያደረጉ መሆኑን እንዲሁም በቋሚነት የመንገድ ጥገና ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች ስልጠና እየሰጠናቸው እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

73. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ለመ/ቤታአችን በላኩት የድርጊት መርሃ ግብር ላይ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች እስከ 2004 መጨረሻ ድረስ መመሪዎቹን በማሰራጨት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ የገለጸ በመሆኑ ማሰራጨቱ የፅ/ቤቱ ድርሻ አይደለም ተብሎ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

74. የመንገድ ኤጀንሲዎች በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road mentenance, design and standared መመሪያ ያልደረሳቸው በመሆኑ የሚያከናውኑትን የመንገድ ጥገና ስራዎች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዳይሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

75. የኮንሰልታንት ቅጥር በወቅቱ እንደማይፈጸም፣ ከተቀጠሩ በኋላም ከአማካሪ ድርጅት ጋር የተፈረመውን ውል አፈጻጸም ለመከታተል የተዘረጋ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ እንዲሁም በኦዲቱ በተጎበኙ ክልሎች አማካሪ ድርጅቶች ኃላፊነታቸውን በትክክል ለመወጣታቸው በቂ ክትትል እና ቁጥጥር እንደማይሠሩ፣ በውላቸው መሰረት ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን የሰው ኃይል እና ሎጂስቲክ በማሟላት ስራውን እያከናወኑ አለመሆናቸው ለዚህም ዋናው ምክንያት አማካሪ ድርጅቶቹ በውላቸው ላይ በተቀመጠው መሰረት የመንገድ ጥገና መከናወኑ የመከታተል እና የመቆጣጠር ስራ በበቂ ሁኔታ ባለመሠራቱ፣ ለመንገድ ጥገና መጠቀም የሚገባቸውን ግብዓት የማይጠቀሙና ደረጃውን የጠበቀ የጥገና ስራና የውሃ

ፍሳሽ ማስወገጃ በአግባቡ ባለመሠራታቸው በከፍተኛ ወጪ የተጠገኑ መንገዶች ማገልገል ከሚገባቸው ጊዜ በታች ግልጋሎት እንዲሰጡ ማድረጉን የታዩ ግኝቶች ነበሩ፡፡

76. የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚገመግሙ አማካሪዎች በወቅቱ ተቀጥረው ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገባ ይገባል፡፡

77. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት የፕሮጀክቶች አፈፃፀም የሚገመግሙ አማካሪዎች በወቅቱ መቀጠራቸውንና በገቡት ውል መሰረት ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣታቸውን ኮንትራቱን የሚያስተዳድሩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ተገቢውን እንዲፈጽሙ ከሚያዚያ ወር 2004 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2004 ዓ.ም ድረስ የመከታተል ስራዎች እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

78. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ፡-

- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚቀጠሩ አማካሪዎች ቢጋር (Terms of Reference) TOR በፅ/ቤቱ ተከለሶ መዘጋጀቱን፣
- በ2007 በጀት አመት የትግራይ ክልል ኮንስትራክሽንና መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ የአማካሪ (የኮንሰልታንት) ቅጥር በወቅቱ የማይፈጸም መሆኑ፣
- በ2006 በጀት አመት በደቡብ መንገዶች ባለስልጣን ከተሞች ከአማካሪዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክትትል እና ድጋፍ ሳያገኙ የሚሰሩ ስራዎች ጥራት እና ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን ሳይረጋገጥ እየሰሩ መሆኑ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቱ ከእቅድ አወጣጥ ጀምሮ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ክትትልና ሙያዊ እገዛ ባለማድረጉ የጥገና መስመሮች ተለይተውና ለተለያዩ የጥገና መስመሮች ተገቢ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ የጥገና ስልት በመለየት ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ማድረጉ እንዲሁም በሆሳዕና መዘጋጃ ቤት አማካሪው ድርጅት ዘግይቶ የተቀጠረ በመሆኑ በቂ ክትትልና ዕገዛ ያላደረገና ክፍያ ለማጸደቅ ብቻ የሚገኝ መሆኑ፣

- በ2008 በጀት አመት ከኮንሰልታንት ጋር በተያያዘ በደቡብ ክልል መንገድ ባለስልጣን ዲስትሪክት የሚጠገነው የጫንጮ ጪንቻ መንገድ በዳቤክ ኮንሰልታንት አማካሪነት የተያዘ ቢሆንም የሚያስፈልጉ የቴክኒክና ፕራክቲካል የመንገድ ስራ ሂደቶችን ቀርጾ መተግበር ሲገባው በቦታው ፈጽሞ እንደማይገኝና ስራውንም እንደማይከታተል ፣
- በ2009 በጀት አመት በደቡብ/ብ/ብ/ሕ መንገዶች ባለስልጣን ፡-ሆሳዕና ዲስትሪክት የኮንሰልታንት ቅጥር የተፈጸመ ቢሆንም ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸውና የቴክኒክ እርዳታ እንደማይደረጋላቸው፣ በአርባ ምንጭ ዲስትሪክት ከአማካሪ ድርጅቱ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ እንደማያደርግ፣ ጉበሬ ዲስትሪክት አማካሪ ድርጅቱ በቂ የሆነ ድጋፍ እንደማያደርግ፤
- በ2006 በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን በኩል የጥገና መስመር በሚመረጥበት ወቅት እና የተመረጡ መንገዶች የሚመረጥላቸው የጥገና አይነት ላይ ክፍተት መኖሩ ለዚህም ምክንያት የሆነው አማካሪው በገባው ውል መሰረት በእቅድ የተያዙትን መስመሮች ለይቶ የተመደበላቸው የጥገና ዘዴ ተገቢ መሆኑን ማረጋገጥ እና የተለዩ ክፍተቶችን ለመንገድ ፈንድ ሪፖርት ማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩ፣እንዲሁም በአምቦ ከተማ መዘጋጃ ቤት የመስመር ጥገና ስራው በራሳቸው ሰርተው አጠናቀው የቆዩ ቢሆንም ስራው በአማካሪ ታይቶ ክፍያ እንዲፈጸም የሚያስችለው አማካሪው በመሆኑ የአማካሪው ድርጅት ቅጥር በመዘግየቱ ክፍያውን በወቅቱ መጠየቅ እንዳይችሉ ማድረጉ፤
- በ2005 በጀት አመት በአማራ የገጠር መንገዶች ባለስልጣን፣ በደብረ ታቦር ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ እንዲሁም በፍኖተ ሰላም ከተማ ማዘጋጃ ቤት አማካሪ ድርጅት የተቀጠረ ቢሆንም ምንም ድጋፍና እገዛ ሳያደርግ የመንገድ ጥገና ስራዎቹ ተሰርተው ከተጠናቀቀ በኃላ የክፍያ ሰርተፍኬት ለማጽደቅ ብቻ እንደሚመጣና ስራቸውን እያከናወኑ ስለመሆናቸው ክትትል የሚደረግበት ስርዓት የሌለ መሆኑ፣ ከተከለሱ ማስረጃዎች የታየ ሲሆን፣
- በናሙና ተመርጠው በመስክ በታዩ ወሊሶ፣ ጅማ ፣ ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤቶች፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የጅማ ዲስትሪክት አማካሪ ድርጅቱ በከተማዎቹ ጽ/ቤት እንደሌለውና በስልክ ሲጠራ ብቻ እየመጣ እንደሚሰራ ክትትልና ድጋፉ በቂ እንዳልሆነ እና አማካሪ ድርጅቱን

ለመቆጣጠር ምንም የተዘረጋ ስርዓት እንደሌለ፣ አማካሪ ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ስራዎች በመለየትና በጣም ለተጎዱ የመንገድ ክፍሎች ቅድሚያ በመስጠትና ጥገና የሚፈልጉትን የመንገድ ክፍሎች እና የጥገና አይነቶችን በመለየት የውለታ ሰነዱ በሚያዘው መሰረት ለኮንትራክተሩ የስራ ትእዛዝ በመስጠት ስራዎቹ እንዲከናወኑ አለማድረግ፣ ከአማካሪዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክትትል እና ድጋፍ ሳያገኙ የሚሰሩ ስራዎች ጥራት እና ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን ሳይረጋገጥ እየሰሩ መሆኑ

የታዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

90. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ አማካሪዎችን የሚቀጥሩት የመንገድ ኤጀንሲዎች በመሆናቸው ኮንትራት ማስተዳደርና አማካሪዎችንም መቆጣጠር የመንገድ ኤጀንሲዎች ኃላፊነት መሆኑን ነገር ግን ፅ/ቤቱ በራሱ መከታተያ መንገዶች በመስክ ምልከታ እንደሚያይ ገልፀዋል፡፡

91. ኃላፊዎቹ ይህንን ቢሉም አማካሪዎች ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ሰፊ በመሆናቸው፣ በፅ/ቤቱ የሚሰሩ የመስክ ምልከታ ሪፖርቶች ካሉት የመንገድ ኤጀንሲዎች አንፃር አነስተኛ መሆናቸው እና በተሰሩ የመስክ ምልከታ ሪፖርቶች ላይ በሚገኙ ግኝቶች ላይ እርምጃ እንዲወስዱ የተደረገበትን ማስረጃዎች ያልቀረቡ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያቸግራል፡፡

92. የአማካሪዎች ቅጥር በወቅቱ የማይፈጸም መሆኑ አማካሪ ድርጅቱ ከእቅድ አወጣጥ ጀምሮ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ክትትልና ሙያዊ እገዛ እንዳያደርጉ እና በዚህም የጥገና መስመሮች ተለይተውና ለተለያዩ የጥገና መስመሮች ተገቢ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ የጥገና ስልት በመለየት ላይ ክፍተት እንዲፈጠር የሚያደርግ ሲሆን የተቀጠሩ አማካሪዎች ለመንገድ ኤጀንሲዎች የቴክኒካል ክትትል እና ድጋፍ ማድረጋቸው ሳይረጋገጥ እየሰሩ በመሆኑ የመንገዶች የጥራት ደረጃ ዝቅተኛ እንዲሆን ብሎም የአማካሪ ድርጅቶቹም ኃላፊነታቸውን ሳይወጡ ክፍያ እንዲፈፀምላቸው ያደርጋል፡፡

## የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መኖሩን በተመለከተ

93. በቀደመው ኦዲት ወቅት በጽ/ቤቱ የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ካለመደረጉም በላይ ለመንገድ ጥገና ለተከፈለው ወጪ ተመጣጣኝ

አገልግሎት መገኘቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩን እና በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች ላይ የሚደረገው ወቅታዊ ክትትልም ጠንካራ አለመሆኑ የሚለው የተገኘ ግኝት ነበር፡፡

94. የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት ጽ/ቤቱ የሚከናወኑ የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎችን በየዓመቱ በማቀድ የፋይናንሻል እና የቴክኒክ ኦዲት ማከናወን አለበት የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ፅ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

95. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት የፋይናንስና የቴክኒክ ስራዎች እንዲሁም የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመፈተሽ እስከ ሰኔ 2004 ዓ.ም ድረስ ደካማ ጎኖችን ለማሻሻል የሚያስችል ስራ እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

96. በክትትል ኦዲቱ ወቅት

- በፅ/ቤቱ የውስጥ የቴክኒካል ክትትልና ግምገማ ቡድን የተካሄዱ የመስክ ግምገማ ሪፖርቶች መኖራቸው፣
- ክፍያዎች በሚጠየቁበት ጊዜ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ፣ የአማካሪው ሪፖርት እና ክፍያዎች የድምር ስህተት የሌለበት መሆኑ እየታዩ መፅደቃቸው፣
- የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች በእቅድ ተይዘው እየተሰራባቸው መሆኑ፣
- በፅ/ቤቱ የውስጥ የፋይናንሻል ኦዲት ክፍል በመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ የመስክ ምልከታ በማድረግ የክትትል ሪፖርቶች መኖራቸው እና
- በኦዲት ኮርፖሬሽን አማካኝነት በመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ በየዓመቱ በሚሰሩ ኦዲት ስራዎች እና በመንገድ ኤጀንሲዎች በሚቀርቡ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ግብረ መልስ መስጠታቸው

ከተስተካከሉ ስራዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት የታዩ ናቸው፡፡

97. ነገር ግን

- የመስክ ግምገማ ሪፖርቶቹ ወጥ የሆነ ፎርማት ያልተከተሉ መሆናቸው፣
- አብዛኛውን የመንገድ ኤጀንሲ የማይሸፍኑ፣ ተከታታይነት የሌላቸው እና በፅ/ቤቱ ቴክኒካል ኦዲት ክፍል በመስክ ምልከታው ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ፣

- ከኦዲት ኮርፖሬሽን ሪፖርት በመነሳትም ሆነ በውስጥ በተሰሩ ፋይናንሻል ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች የተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው ከተሰብሳቢ ሂሳብ በስተቀር ሌሎች ግኝቶች ላይ የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ፣

እንደ ክፍተት የታዩ ናቸው፡፡

98. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ ፣ በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ የመንገድ ኤጀንሲዎች እንደ መንግስት አካል ሃላፊነት የሚወስዱ መሆኑን፣ በፅ/ቤቱ የመስክ ምልከታና ግምገማ በናሙና ላይ የተመሰረተ መሆኑ ለዚህም ሃገሪቱ ከ110 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ መንገድ መኖሩና በመደበኛነት ቁጥጥር የሚያደርግ ሰው ለመመደብ ስለማይቻል የመንገድ ጥገናው ለተከፈለው ወጪ ተመጣጣኝ አገልግሎት መገኘቱን ለማረጋገጥ 1ኛ የመንገድ ኤጀንሲዎቹን የመቆጣጠር አቅም በስልጠና እያጠናከሩ መሆኑ፣ 2ኛ የመንገድ ጥገና የሚያካሂዱ አማካሪዎችን በመቅጠር፣ 3ኛ ዩንቨርስቲዎች የመንገድ ጥገና ጥራት መጠበቁን እንዲያረጋግጡ እየተደረገ መሆኑ ፣ 4ኛ የፅ/ቤቱ መሃንዲሶች መደበኛና ድንገተኛ የመስክ ምልከታ እያደረጉ ክትትል እያደረጉ እንደሚገኙ እንዲሁም 65 ፐርሰንት በጀት የሚመደበው ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ 25 ፐርሰንት ለክልል መንገድ ባለስልጣናት 10 ፐርሰንት ለከተሞች ( 5 ፐርሰንት ለ59 ከተሞች፣ 5 ፐርሰንት ለአዲስ አበባ ) የሚመደብ በመሆኑ ትንንሽ በጀት የሚመደብላቸውን በሙሉ ፅ/ቤቱ ካለው የሰው ኃይል አንፃር ማየት እንደማይችሉ ከዚህ በተጨማሪም በየአመቱ የሂሳብ ምርመራ ኮርፖሬሽን መቶ በመቶ የሁሉንም ኤጀንሲዎች ሂሳብ ምርመራ ስለሚያከናውን ከግኝቶቹ በመነሳት ችግሮች የጎሉባቸው ላይ የውስጥ ኦዲት በተለየ ክትትል የሚያደርግባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

99. ኃላፊዎቹ ይህንን ይበሉ እንጂ ተሰሩ የተባሉ ስራዎች ካሉት የመንገድ ኤጀንሲዎች አንፃር አነስተኛ እና በተከታታይነት ያልተከናወኑ በመሆኑን ሁሉንም መሸፈን ካልቻሉ ሌላ አማራጭ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ወይንም ዘዴ በመዘርጋት ማረጋገጥ የነበረባቸው በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

100. የመስክ ግምገማ ሪፖርቶቹ ወጥ የሆነ ፎርማት እንዲከተሉ፣አብዛኛውን የመንገድ ኤጀንሲ እንዲሸፍኑ፣ ተከታታይነት ኖሯቸው እና በመስክ ምልከታው ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ ክፍተቶችን በመለየት በተለዩ

ክፍተቶችን ላይ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን የምናረጋግጥበት ሁኔታ እንዳኖር ያደርጋል፡፡

## በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት መከናወኑን በተመለከተ

101. ጽ/ቤቱ ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት ካከናወናቸው የክትትል እና የቁጥጥር ስራዎች ዋና የሆነውን በመንገድ ኤጀንሲዎች የተከናወኑ የፊዚካል እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንሻልም ሆነ የቴክኒካል ኦዲት አላከናወነም የሚለው የኦዲቱ ግኝት ነበር፡፡

102. በመሆኑም በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት በእቅድ በመያዝ መከናወን አለበት የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

103. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱም በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት ከዚህ በፊት ሲከናወን የነበረውን የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት እቅድና አፈጻጸም ክፍተቶችን ገምግሞ ለመለየት እስከ 2004 ዓ.ም ጥናት በማድረግ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀዋል፡፡

104. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ በፅ/ቤቱ፡-

- የፋይናንሻል ኦዲት በ2007 በጀት ዓመት 29 ኦዲት ለመስራት ታቅዶ 8 ኦዲት (27.6 %) መከናወኑ የተገለፀ መሆኑ፣ በ2008 በጀት አመት 30 ኦዲት ለመስራት ታቅዶ 20 ኦዲት (66.6 %) መሰራቱ የተገለፀ መሆኑ እና በ2009 በጀት ዓመት 10 ኦዲት ለመስራ ታቅዶ እስከ ግንቦት 30 ድረስ 5 ኦዲት(50 %) መከናወኑ የተገለፀ ቢሆንም በ2007 በጀት አመት 1 አዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ላይ የተሰራ ኦዲት፣ በ2008 በጀት አመት 6 የመንገድ ኤጀንሲዎች እና 1 ፖስታ ቤት ላይ የተሰራ ኦዲት፣ በ2009 በጀት አመት ደግሞ 3 የመንገድ ኤጀንሲዎች፣ 1 ፖስታ ቤት እና 1 ኮሜት ትራንስፖርት ላይ የተሰራ ኦዲት ሪፖርት ቀርቧል ይህም ተሰርቷል ከተባለው 33 ኦዲት ሪፖርት ውስጥ 16ቱ ብቻ ማስረጃ የተያያዘላቸው ሲሆን ሌሎቹ ከላይ በአፈፃፀም የቀረቡ ኦዲት ሪፖርቶች ማስረጃ ያልቀረበባቸው መሆኑ፣

- እንዲሁም ቴክኒካል ኦዲትን በተመለከተ አፈጻጸሙን ለመለካት የሚያስችል ዕቅድና አፈጻጸም ሪፖርት ባይኖርም በቴክኒካል ክፍል በ2009 ዓ.ም አንድ ቴክኒካል ኦዲት ብቻ የተሰራ እና በውጭ ፅ/ቤቱ ያሰራቸው በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሲቪል ምህንድስና ትምህርት ክፍል በ2004 እና በ2009፣ በ2008 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ሲቪል ምህንድስናና ቴክኖሎጂ ትምህርት ክፍል የተሰሩ 3 ቴክኒካል ኦዲት ሪፖርቶች ብቻ መኖራቸው ከተከለሱ ማስረጃዎች ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣
- እንዲሁም በመስክ በናሙና ተመርጠው ከታዩ ወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት፣ ጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት እና በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ጅማ ዲስትሪክት መንገድ ጥገና ቅርንጫፍ ፅ/ቤት የጽ/ቤቱ ባለሙያዎች በተሰሩ ስራዎች ላይ ቴክኒካሊ በማየት እዚያው አስተያየት ከመስጠት ባለፈ ቴክኒካል ኦዲት ተሰርቶ እንደማያውቁ መግለፃቸው ታይቷል፡፡

105. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች በኦዲት ኮርፖሬሽን ኦዲታቸው የሚከናወን በመሆኑ እና ጽ/ቤቱ ያለው የሰው ሀይሉ ከሚጠገኑ የመንገድ ብዛት አንጻር አነስተኛ በመሆኑ ማከናወን አለመቻላቸውን ቢገልጹም ኤጀንሲው በዕቅድ የያዛቸውን የኦዲት ሥራዎች ማከናወን ባለመቻሉ ምክንያቱን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

106. በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ የፋይናንስና የቴክኒክ ኦዲት ሪፖርቶች አነስተኛ መሆን በፅ/ቤቱ ፈንድ ተጠቃሚ በሆኑ የመንገድ ኤጀንሲዎች ያሉትን ክፍተቶች እንዳይለዩ እና በተገኘው ውጤት መሰረት ግብረ መልስ ሰጥቶ ቁጥጥርና ክትትል እንዳይደረግባቸው ያደርጋል፡፡

## በጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች የጥገና ታሪክ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ መኖሩን በተመለከተ

107. የጽ/ቤቱ ሁሉም በመንገድ ኤጀንሲዎች ስለሚያስተዳድሯቸው መንገዶች የሚገልጽ (የመንገዶችን አይነት፣ ርቀት፣ ደረጃ ፣የጥገና ታሪክ፣ በምን ያህል ወጪ እና መቼ እንደተጠገኑ...) የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ተይዞ አልተገኘም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የጥገና ታሪክ የሚገልጽ መረጃ በመስክ ጉብኝት በታዩት የመንገድ ኤጀንሲዎች ጭምር ተይዞ አለመገኘቱ የታየ ክፍተት ነበር፡፡

108. በመሆኑም ጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን፣ በምንያህል ወጪ መቼ እንደተጠገኑ የሚያሳይ

የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ ሊይዝ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

109. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱ በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በኦዲቱ ወቅት በተሰጠው ማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት በፅ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ስር ስለሚገኙ መንገዶች የጥገና ታሪክ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ ሆነ መረጃ እንዲኖር የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ በመውሰድ የትኞቹ መረጃዎች በጽ/ቤቱ እንዲሁም የትኞቹ መረጃዎች በመንገድ ኤጀንሲዎች መቀመጥ እንዳለበት በመለየትና ጥናት በማድረግ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ዙሪያ ያለው ክፍተት ተጠንቶ የማስተካከያ ስራ እንደሚሰራ ገልፃዋል፡፡

110. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን፣ በምንያህል ወጪ መቼ እንደተጠገነ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ በተደራጀና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተይዞ የማይገኝ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩ በአንዳንድ የመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ መረጃዎቹ ተሰርቷል ተብሎ የቀረበ ቢሆንም በተሟላና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ያለመያዝ ክፍተት መኖሩ ታይቷል፡፡

111. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ መረጃዎቹ የመንገድ ኤጀንሲዎች ቢይዙት የተሻለ እንደሚሆንና ፅ/ቤቱም የመንገድ ኤጀንሲዎቹ በሚልኩት መሰረት በየአመቱ እየመዘገቡ እንደሚገኙ በተጨማሪም በአገሪቱ ያሉትን መንገዶች ከነደረጃቸው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በኩል ተጠንቶ የሚገኝ በመሆኑ መረጃውን ፅ/ቤቱ እየተገለገለበት እንደሚገኝ እና መረጃዎች መያዛቸው በአገሪቱ ያሉ መንገዶች ያሉበትን ደረጃ እንዲለዩ እንደሚያደርጋቸው እና አሁን ላይ ከላይ በተጠቀሱት መሰረት ማስረጃዎችን በዳታ ቤዝ የመስራት ስራ በፅ/ቤቱ በሂደት ላይ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

112. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ የሰጡ ቢሆንም ፅ/ቤቱ በኦዲቱ ወቅት በተሰጠው ማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት በፅ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ስር ስለሚገኙ መንገዶች የጥገና ታሪክ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ ሆነ መረጃ እንዲኖር የሌሎች ሀገሮችን ተሞክሮ በመውሰድ የትኞቹ መረጃዎች በጽ/ቤቱ እንዲሁም የትኞቹ

መረጃዎች በመንገድ ኤጀንሲዎች መቀመጥ እንዳለበት በመለየትና ጥናት በማድረግ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ዙሪያ ያለው ክፍተት ተጠንቶ የማስተካከያ ስራ እንደሚሰራ ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር ከገለጸው ጋር የተሰጠው ምላሽ የሚቃረን በመሆኑ እና ከመንገድ ኤጀንሲዎች የሚላከውን እየመዘገብን እንገኛለን ለሚለው የተሟላ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

113. ጽ/ቤቱ ከተለያዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ ባለመያዙ መንገዶች ያሉበትን ደረጃ እንዳይታወቅና በጥገና ሽፋን መካተት ያለባቸው ሁሉም መንገዶች እንዳይለዩ እና ከመረጃዎቹ በመነሳት ፍትሃዊ የበጀት ድልድል ለፈንዱ ተጠቃሚዎች እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡

## የመንገድ ደህንነት ስራ ስለመሰራቱና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

114. የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ደህንነት ዙሪያ እንዳልሠሩና በሚመለከታቸው አካላትም ቢሆን መሠራት ያለበትን ያህል አለመሠራቱን የመስክ ጉብኝት በተደረገባቸው አውራ መንገዶች ላይ በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የተሠራው ሥራ አጥጋቢ አለመሆኑን፣ በጽ/ቤቱም በኩል ለመንገድ ኤጀንሲዎች ሥራውን እንዲያከናውኑ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አለመደረጉና በጀትም እንዳልተያዘ በኦዲቱ የታዩ ግኝቶች ነበሩ፡፡

115. በመሆኑም ጽ/ቤቱ የመንገድ ኤጀንሲዎች በፈንዱ የመንገድ ደህንነት ስራ ማከናወን ይችሉ ዘንድ እና በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ፅ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልኩ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

116. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱም በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ በማሻሻያ ሃሳቡ መሰረት የመንገድ ደህንነት ስራው መሰራቱንና መረጋገጡን ስራ በመንገድ ደህንነት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የሚተገበር ቢሆንም የመንገድ ፈንድ በጀቱን እንደሚመድብ አካል ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ የበጀት አፈጻጸሙ ላይ ተገቢውን ክትትል እንደሚያጠናክር ገልፀዋል፡፡

117. ይሁን እንጂ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በመንገድ ፈንድ ፅ/ቤትም ለመንገድ ካውንስል ለመንገድ ደህንነት ስራዎች ፈንድ የሚመድብ ቢሆንም በ2007፣ በ2008 እና

በ2009 የተመደበ በጀት 13,600,000 ብር፣ 13,600,000 ብር እና 17,680,000 ብር ሲሆን ስራ ላይ የዋለ በጀት ደግሞ 0ብር ፣0 ብር እና 6,452,100ብር ነው ይህ ማለትም እንደቅደም ተከተላቸው ሲቀመጥ 0%፣ 0% እና 36.49% ሲሆን የተመደበው ፈንድ ለታለመለት አላማ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ የማይደረግ መሆኑ ለዚህም አፈፃፀም በማይኖርበት ወይም ዝቅተኛ አፈፃፀም በሚኖራቸው ጊዜ ምንም አይነት ግብረ መልስ ለመንገድ ካውንስል የማይላክ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከከለስናቸው ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

118. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት እና በክትትል ኦዲቱ ረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ እንደ መንገድ ኤጀንሲዎቹ ሁሉ የመንገድ ካውንስልም አፈፃፀም ከሌላቸው ፅ/ቤቱ በጀት እንደማይለቅላቸው ነገር ግን የካውንስል ፅ/ቤቱ ቀደም ብሎ የአደረጃጀትና የሰው ኃይል እጥረት የነበረበት በመሆኑ የሚመደበውን በጀት በአግባቡ አለመጠቀሙ፣ የእቅድ እና የእቅድ አፈፃፀም መድረክ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ሲዘጋጅ የመንገድ ካውንስልም ምክክር እንዲያደርጉ መደረጉን እንዲሁም በትክክል የተመደበውን በጀት ለሚፈለገው አላማ እንዲያውሉ፣ አፈፃፀማቸውን በየጊዜው እንዲያቀርቡ እና የወሰዱትን ገንዘብ በትክክል እንዲያወራርዱ ውይይት መደረጉን እና በአሁኑ ወቅት መሻሻሎች እየታዩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተጠቀሱት ግኝቶች ከመነሳት አፈፃፀሙ ስለመሻሻሉ የኦዲት ቡድኑ ለመቀበል ይቸገራል፡፡

119. ጽ/ቤቱ ለመንገድ ካውንስል ጽ/ቤት ለመንገድ ደህንነት ስራ ማከናወኛ በየዓመቱ ለሚመድበው በጀት ለታለመለት አላማ መዋሉን ክትትል እንዲሁም ዕቅድ አፈጻጸሙን ግምገማ የማያደርግ በመሆኑ የሚመደበውም በጀት ጥቅም ላይ እንዳይውል እና የመንገዶች ደህንነት እንዳይጠበቅ ያደርጋል፡፡

## ጽ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት በተመለከተ

120. ጽ/ቤቱ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳውቅ መረጃ አዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው አለማድረጉ ፤ በዚህም ምክንያት በሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት፣ በመንገድ ኤጀንሲዎችና በአማካሪ ድርጅቶች በኩል ግልጽ የሆነ እና የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ በመንገድ ኤጀንሲዎች እና በጽ/ቤቱ መካከል የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖር እና ጠንካራ

የቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ፈንድ ከመስጠቱ በፊት ውል ያልተዋዋለ እና ለኤጀንሲዎች የሚፈጸሙ ክፍያዎችም በውሉ መሰረት እንዲፈጸሙ አለመደረጉ የተገኙ ግኝቶች ነበሩ፡፡

121. በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በመንገድ ኤጀንሲዎች፣ በአማካሪ ድርጅቶች፣ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት፣ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የሚገልጽ መረጃ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ማድረግ እና ጽ/ቤቱ በመንገድ ደህንነት ፕሮግራሞች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስራዎችን በማከናወን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት የሚል የማሻሻያ ሃሳብ ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ ፅ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊልክ እና በመርሃ-ግብሩ መሰረት ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡

122. የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤቱ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ልኳል፡፡ ፅ/ቤቱም በላከው የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የማሻሻያ ሃሳቡን በተመለከተ ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና ከመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ስላለው የስራ ግንኙነት በበቂ ሁኔታ በፈንዱ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተገለጸ በመሆኑ ይህንን ዶክመንቶችና መመሪያዎች ሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲያውቁት እስከ ሰኔ 2004 ዓ.ም ድረስ እንዲደርሳቸው እንደሚደረግ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መሰጠቱን በተመለከተ ህብረተሰቡ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት መንገዶቹ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የመከላከል ስራ እንዲያከናውኑና እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ስለ ጉዳዩ ህብረተሰቡ ተገቢውን ግንዛቤ እንዲያገኝ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ተገቢውን ስራ እንደሚሰራ ላይ ገልፃል፡፡

123. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጽ/ቤቱ በ 2005 በጀት አመት በጽ/ቤቱ እና በዜጎች (ደንበኞች፣ባለድርሻ አካላት፣ተባባሪ አካላትና ሌሎች) መካከል የተጠናከረ ግንኙነት እንዲኖር እና ግልጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ አሰራር ለማስፈን የዜጎች ቻርተር የተዘጋጀ ሲሆን በተጨማሪም በ2009 በጀት አመት በጽ/ቤቱ በመንገድ ኤጀንሲዎች ለመንገድ ጥገና ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለሚቀጠሩ አማካሪዎች መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን በክትትል ኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች ጅማ፣ ወሊሶ እና ወልቂጤ ማዘጋጃ ቤቶች ጽ/ቤቱ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳውቅ መረጃ ወይም መመሪያ እንዳልደረሳቸው፣ አማካሪው ድርጅት

በክልል መንገድ ባለስልጣን ተቀጥሮ ሲመጣ አንድ ደብዳቤ ብቻ ይዞ በመምጣት ስራ እንደሚጀምር በተጨማሪም በዓመት አንድ ግዜ የምክክር መድረክ ከማዘጋጀት ሌላ ወጥ የሆነ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እንደማይሰጥ ገልፀዋል፡፡

124. ስለጉዳዩ የፅ/ቤቱ የስራ ሃላፊዎች በቃለ መጠይቅ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ መረጃዎች እንዴት ይተላለፋሉ የሚለው ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች የአማካሪ ቅጥር ሲፈፀም ያለው የስራ ሃላፊነት ለየከተማዎቹ እንዲልኩ ማሳሰቢያ እንደሰጡና በአመት ሁለት ጊዜ የምክክር መድረክ ላይ በሚያደርጉት ውይይት ወቅት ከእያንዳንዱ ባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ ጥልቅ ውይይት እንደሚያደርጉ ከዚህ በተጨማሪ መንገድ ኤጀንሲዎች በጀት ሲጠቀሙ የመንገድ ፈንድ ቦርድ ባፀደቀው የበጀት አስተዳደርና ፋይናንስ መመሪያ መሰረት ስራ ላይ የሚውል ሲሆን በጀት ተጠቃሚ የመንገድ ኤጀንሲዎችም ለሚያገኙት አገልግሎት ማሟላት ያለባቸውንና ፅ/ቤቱ የሚሰጣቸውን አገልግሎት በዜጎች ቻርተር ወጥቶ የመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲያውቁት መደረጉን በጋራ ምክክር መድረኮችም በአፈፃፀም ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመፍታት የተሳለጠ አሰራር እንዲዘረጋ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

125. ኃፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የዜጎች ቻርተሩ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች ስለመሰራጨቱና ስለመድረሱ፣ እንዲሁም በሚዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ስለመጠራታቸው እና ስለመገኘታቸው ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

126. በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት እና በመንገድ ኤጀንሲዎች፣ በአማካሪ ድርጅቶች፣ እና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት፣ ያላቸውን የስራ ድርሻ፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የሚገልጽ መረጃ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ ባለመደረጉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ያላቸውን የስራ ሃላፊነት በግልፅ እንዳያውቁትና ከተጠያቂነት አንፃር ያለባቸውን ግዴታ እንዳይረዱት ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

127. በመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት የመንገድ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ ኦዲት ተከናወኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እንዲሁም እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

### 3.1 እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- ድንበር አቋርጠው ከሱዳን ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ በወጋገን ባንክ በኩል የሚሰበሰው ገቢ 2009 በጀት አመት ላይ መዘግየት ያልታየ መሆኑ፡፡
- በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ ገቢ ለማስፈፀም በየካቲት 340/2007 ደንብ መውጣቱ እንዲሁም ፅ/ቤቱ ከፖስታ ቤት አገልግሎት ድርጅት ጋር ውል በመዋዋል ከመስከረም 2008 ጀምሮ ገቢዎች እየተሰበሰቡ መሆኑ ለመንገድ ጥገና እና ደህንነት ጥበቃ የሚውል ተጨማሪ ገቢ እንዲገኝ የሚያደርግ ሆኖ ታይቷል፡፡
- በፅ/ቤቱ የቴክኒካል ኦዲት ክፍል ለብቻው መዋቀሩ፡፡
- ከሚመደበው በጀት ጋር የተጣጣመ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ስራ እና የፋይናንስ እቅድ መዘጋጀትና መቅረቡን በተመከተ ፅ/ቤቱ በ3 አይነት አማራጮች የፊዚካልና የፋይናንሻል እቅድ እንዲያዘጋጁ የሚያሳስብ ደብዳቤ እና የእቅድ አቀራረብ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚልክ መሆኑ እና የመንገድ ኤጀንሲዎች የፋናንሻልና የፊዚካል እቅዳቸውን ለፅ/ቤቱ በሚልኩበት ጊዜ በተላከላቸው መስፈርት መሰረት ማቀዳቸውን በቴክኒካል ግምገማ እና ክትትል ባለሙያዎች እየተገመገመ እቅዳቸው የሚፀድቅ መሆኑ ስራዎች በእቅዱ መሰረት እንዲሳኩ እያደረገ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡
- የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በተመለከተ በፅ/ቤቱ የውስጥ የቴክኒካል ክትትልና ግምገማ ቡድን የተካሄዱ የመስክ ግምገማ ሪፖርቶች መኖራቸው፡፡ ፣ በፅ/ቤቱ 1 የቴክኒካል ኦዲት እና በውጭ ዩንቨርስቲዎችን ቀጥረው ያሰሯቸው 3 የቴክኒካል ኦዲት ሪፖርቶች መኖራቸው፤ ክፍያዎች በሚጠየቁበት ጊዜ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የአማካሪው ሪፖርት እየታዩ መፅደቃቸው፣ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎች በእቅድ ተይዘው እየተሰራባቸው መሆኑ፣ በፅ/ቤቱ የውስጥ የፋይናንሻል ኦዲት

ክፍል በመንገድ ኤጀንሲዎች ፣በፖስታ ቤት እና በኮሜት ትራንስፖርት ላይ የተሰሩ የተወሰኑ የኦዲት ሪፖርቶች መኖራቸው እና በኦዲት ኮርፖሬሽን በመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ በሚሰሩ ኦዲት ስራዎች እንዲሁም በመንገድ ኤጀንሲዎቹ በውስጥ ኦዲት ለሚሰሩ የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ግብረ መልስ መስጠታቸው

- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚቀጠሩ አማካሪዎች ቢ.ጋር (Terms of Reference) TOR በፅ/ቤቱ ተከለሶ መዘጋጀቱ፣
- ጽ/ቤቱ በ 2005 በጀት አመት በጽ/ቤቱ እና በዜጎች (ደንበኞች፣ባለድርሻ አካላት፣ተባባሪ አካላትና ሌሎች) መካከል የተጠናከረ ግንኙነት እንዲኖር እና ግልጽነትና ተጠያቂነት የተላበሰ አሰራር ለማስፈን የዜጎች ቻርተር ያተዘጋጀ ሲሆን በተጨማሪም በ2009 በጀት አመት በጽ/ቤቱ በመንገድ ኤጀንሲዎች ለመንገድ ጥገና ክትትልና ቁጥጥር ስራ ለሚቀጠሩ አማካሪዎች መመሪያ የተዘጋጀ መሆኑ

## 3.2 እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- በኢትዮጲያ ነዳጅ ድርጅት በኩል እየተሰበሰበ የሚገኝ ለመንገድ ጥገና ከተጣለ የነዳጅ ታሪፍ እና በነዳጅ ማደያ ድርጅቶች በኩል የሚሰበሰብ ከቅባትና ዘይት መሰብሰብ ያለበት ገቢ ወቅቱን ጠብቀው ገቢ የማያስገቡ መሆኑ፡፡
- ድንበር አቋርጠው ከጅቡቲ ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ጠቀሜታ ክፍያ ገቢ በኮሜት ትራንስፖርት(የኢትዮጲያ ባህር ትራንዚት አክሲዮን ማህበር) በኩል የሚሰበሰብ ሲሆን ለፅ/ቤቱ የሽያጭ ሪፖርት የማይቀርብ፣ የመቼ ወር የተሰበሰቢ ገቢ እንዳስገቡ የማይገለፅ እና የሰበሰቡትን ገቢ ወደ ፅ/ቤቱ አካውንት ዘግይቶ የሚያስገቡ መሆኑ፡፡
- ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ የ2008 እና የ2009 በጀት አመት ተሰብሳቢ ሂሳብ ወደ ፅ/ቤቱ ምንም አይነት ገቢ ያላስገቡ መሆኑ፡፡ ፅ/ቤቱ ከላካቸው ኩፖኖች ከ2005-2009 በጀት አመት ብዛታቸው 25256 ኩፓን የሚሆኑ ማለትም በአንድ ኩፓን ዋጋ 15 ዶላር በወቅቱ አማካኝ የምንዛሪ ተመን መሰረት(1 ዶላር በ 22.8874 ብር) 8,670,662.62 ብር ገቢ ያላደረገ መሆኑ ፤በተጨማሪም ከኩፓን ቁጥር 040501 — 041500 ብዛታቸው 1000 ኩፓኖች ተሸጦ በሽያጭ ሪፓርት ላይ የቀረበ ቢሆንም ኮሜት ትራንስፓርት አ.ማ ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት ያልተረከበው መሆኑ፡፡

- ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የሚሸጡ ኩፖኖች በወቅቱ ባለው የምንዛሬ ምጣኔ መሰረት መሸጣቸውን በተመለከተ ወጋገን ባንክ አ.ማ በሁመራ ቅርንጫፍ በኩል የሚሸጣቸውን ኩፖኖች በአንዱ ቀን የምንዛሬ መጠን ሁሉንም አስልቶ ገቢ የሚያደርግ

መሆኑ፡፡ ኮሜት ትራንስፖርት ኩፖኖች በትክክለኛው ምንዛሬ መጠን መሸጣቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መቼ እንደተሸጡ የሚያሳይ ማስረጃ አለመያዙ፡፡

- ከነዳጅና ቅባት ከአንድ ሊትር የሚሰበሰበው 10 ሳንቲም የገቢ መጠን ያልተሸሻለ መሆኑ፡፡
- ከተፈቀደው ክብደት በላይ በመጫን ከሚጣል ቅጣት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- በክብደት ላይ ከተመሰረተ አመታዊ የተሽከርካሪ ፈቃድ ማደሻ ክፍያ በአግባቡ እና ወቅቱን ጠብቀው እየተሰበሰቡ አለመሆኑ
- በፈንዱ ገንዘብ ለተሰራው ስራ ተገቢውን ክፍያ መፈጸሙን በተመለከተ የጥገና ስራዎች ተሰርተው ሳይጠናቀቁ እንዳለቁ ተደርጎ ክፍያ የሚጠየቅባቸው አማካሪውም የክፍያ ጥያቄ የሚያፀድቅበት ሁኔታ መኖሩ፣ በአንድ የጥገና መንገድ ላይ በሁለት የተለያዩ የስራ መደቦች ሁለቴ ክፍያ እንደሚፈጸም እንዲሁም አማካሪው ድርጅት የተሰራውን ስራ በመለካት ሳይሆን የነዳጅ ወጪያቸውን ወደ መንገድ ፈንድ ነጠላ ዋጋ ስሌት በመቀየር የሚሰራ መሆኑ፣ አማካሪው ድርጅት በክልል ቢሮ እንደሌለው ክፍያ እንዲያጸድቅ ሲጠየቅ ብቻ እንደሚያፀድቅ ፣መንገድ ኤጀንሲዎች ስር የሚጠገኑ መንገዶች ለመንገድ ጥገና የሚጠቀሙበትን ግብዓት ስለትክክለኝነቱ አማካሪው ላብራቶሪ ቴስት የማያደርግ መሆኑ፣ አማካሪዎች ያላቸው የሰው ሀይል አነስተኛ መሆኑ ይህ ደግሞ ስራዎች ከተሰሩ በኃላ ለመመልከት ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ስራዎችን በቦታው ተገኝቶ እንዲደግፍና ሙያዊ እገዛ በማድረግ ፈንዱ ለታቀደለት ዓላማ እንዲውል አለማስቻሉ፡፡
- በመንገድ ኤጀንሲዎች የሚቀርቡ እቅዶች በፅ/ቤቱ የሚሰጡ የእቅድ ግምገማዎች በበጀት አመቱ እስከ 2ኛ ሩብ አመት የሚዘገዩ መሆኑ
- ለመንገድ ኤጀንሲዎች የሚተላለፈው ገንዘብ በጸደቀው ዓመታዊ እቅድ መሰረት ሥራ ላይ መዋል አለበት የሚለውን በተመለከተ በመንገድ ፅ/ቤት ቦርድ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ፈንድ ያፀደቀው በ2008 እና 2009 እስከ 2ኛ ሩብ አመት መዘግየት የሚታይበት ከመሆኑም በተጨማሪ ለመንገድ ኤጀንሲዎች 20 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፍያ እንዲጠቀሙ የሚፈቀድላቸው ከ1ኛ-4ኛሩብ አመት የሚዘገይ መሆኑ፡፡
- በናሙና በመስክ ከታዩ የመንገድ ኤጀንሲዎች እና ማስረጃ በመከለስ በተገኙ ግኝቶች መሰረት የመንገድ ኤጀንሲዎች በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተዘጋጀ road mentenance, design and standared መመሪያ ያልደረሳቸውና በዛም መሰረት ተግባራዊ እያደረጉ አለመሆኑ

- አማካሪዎች በገቡበት ውል መሰረት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን በተመለከተ የአማካሪዎች ቅጥር በወቅቱ የማይፈጸም መሆኑ፣ ከተሞች ከአማካሪዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክትትል እና ድጋፍ ሳያገኙ የሚሰሩ ስራዎች ጥራት እና ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን ሳይረጋገጥ እየሰሩ መሆኑ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቱ ከእቅድ አወጣጥ ጀምሮ ለመንገድ ኤጀንሲዎች ክትትልና ሙያዊ እገዛ ባለማድረጉ የጥገና መስመሮች ተለይተውና ለተለያዩ የጥገና መስመሮች ተገቢ እና ወጪ ቆጣቢ የሆነ የጥገና ስልት በመለየት ላይ ክፍተት እንዲፈጠር ማድረጉ እንዲሁም አማካሪው በገባው ውል መሰረት በእቅድ የተያዙትን መስመሮች ለይቶ የተመደበላቸው የጥገና ዘዴ ተገቢ መሆኑን ማረጋገጥ እና የተለዩ ክፍተቶችን ለመንገድ ፈንድ ሪፖርት ማድረግ ላይ ክፍተት መኖሩ፣ከአማካሪ ድርጅቱ በቂ የሆነ የቴክኒክ እርዳታ ለመንገድ ኤጀንሲዎች እንደማይደረግላቸው ፣ አማካሪ ድርጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ስራዎች በመለየትና በጣም ለተጎዱ የመንገድ ክፍሎች ቅድሚያ በመስጠትና ጥገና የሚፈልጉትን የመንገድ ክፍሎች እና የጥገና አይነቶችን በመለየት የውለታ ሰነዱ በሚያዘው መሰረት ለኮንትራክተሩ የስራ ትእዛዝ በመስጠት ስራዎቹ እንዲከናወኑ አለማድረግ እንዲሁም ከአማካሪዎች ሊያገኙ የሚገባቸውን ክትትል እና ድጋፍ ሳያገኙ የሚሰሩ ስራዎች ጥራት እና ደረጃቸውን ጠብቀው መሰራታቸውን ሳይረጋገጥ እየሰሩ መሆኑ የታዩ ክፍተቶች መሆናቸው፡፡
- የመንገድ ጥገና የፈንድ አጠቃቀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት በተመለከተ የመስክ ግምገማ ሪፖርቶቹ ወጥ የሆነ ፎርማት ያልተከተሉ መሆናቸው፣ አብዛኛውን የመንገድ ኤጀንሲ የማይሸፍኑ፣ ተከታታይነት የሌላቸው እና በመስክ ምልከታው ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ፣ ከኦዲት ኮርፖሬሽን ሪፖርት በመነሳትም ሆነ በውስጥ በተሰሩ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ላይ ለመንገድ ኤጀንሲዎች በተሰጡ ግብረመልሶች ስለመስተካከላቸው የተጠናከረ ክትትል የማይደረግባቸው መሆኑ እንደ ክፍተት የታዩ መሆናቸው፡፡
- በመንገድ ፈንድ የፊዚካል ሥራ እና የፋይናንስ እቅድ አፈጻጸም ላይ በፅ/ቤቱ ከ2005-2009 1 በውስጥ ኦዲት የቴክኒካል ኦዲት እና በዩንቨርስቲዎች የተሰሩ 3 የቴክኒካል ኦዲት ስራዎች ብቻ እንዲሁም በውስጥ ፋይናንሻል ኦዲት ክፍል ከ2007-2009 በጀት አመት ተሰርተዋል ተብለው ከተገለፁ 33 ኦዲት ሪፖርቶች ውስጥ 13ቱ ብቻ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑ፡፡

- በመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት  የመንገድ ኤጀንሲዎች ሥር ስለሚገኙ መንገዶች አይነት፣ ርቀት፣ የጥገና ታሪክን፣ በምንያህል ወጪ መቼ እንደተጠገነ የሚያሳይ የተሟላ እና ወቅታዊ የሆነ መረጃ በተደራጀና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ተይዞ የማይገኝ  እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩ በአንዳንድ  የመንገድ ኤጀንሲዎች ላይ መረጃዎቹ ተሰርቷል ተብሎ የቀረበ ቢሆንም በተሟላና ዘመናዊ በሆነ መልኩ ያለመያዝ ክፍተት መኖሩ
- ለመንገድ ካውንስል ለመንገድ ደህንነት በሚል ፈንድ ከመመደብ ውጪ የተመደበው ፈንድ  ለታለመለት አላማ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ የማይደረግ መሆኑ  ለዚህም ማሳያ በ2007፣በ2008 እና በ2009 የፋይናንስ አፈፃፀማቸው እንደቅደም ተከተላቸው ሲቀመጥ  0%፣ 0% እና 36.49% ሲሆን አፈፃፀም በማይኖርበት ወይም ዝቅተኛ አፈፃፀም በሚኖራቸው ጊዜ ምንም አይነት ግብረ መልስ ለመንገድ ካውንስል የማይላክ መሆኑ
- ጽ/ቤቱ ከመንገድ ኤጀንሲዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳውቅ መረጃ ወይም መመሪያ ለሁሉም የመንገድ ኤጀንሲዎች እንዲደርሳቸው ያላደረገ መሆኑ፡፡

Office of the Federal Auditor General

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)

128. ከላይ በክፍል ሁለት ላይ የተጠቀሱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች በክፍል ሦስት ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑ ነጥቦች ላይ የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና ማሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክሮ መቀጠል አለባቸው፡፡

129. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ያልተስተካከሉና የእርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት በሚመለከታቸው በሁሉም አካላት የድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶላቸውና አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም የድርጊት መርሃ ግብርም ለመ/ቤታችን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መላክ አለበት፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት እና በናሙና የታዩት አምስት የመንገድ ኤጀንሲዎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ -1-

## አባሪ 1.1 የ2005 ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበ ገቢ

| ተ.ቁ | ገቢ የተሰበሰበበት ድርጅት | የገቢ መጠን | የመቼ ወር እንደገባ | ገቢ የተሰበሰበበት ቀን | ሳይሰበሰብ የዘገየበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | Yetebaberut | 64460.47 | April-june 2013 | 27/8/13 | 4ወር |
| 2. | Ethiopian petroleum supply enterprise (EPSE) | 107000000 | June 2013 | 30/7/13 | 1ወር |
| 3. | EPSE | 107000000 | May 2013 | 2/7/13 | 1ወር |
| 4. | Comet transport | 398824 | የማይታወቅ | 25/10/05 | |
| 5. | Libya oil Ethiopia | 82518 | March 2013 | 25/6/13 | 3ወር |
| 6. | Libya oil Ethiopia | 45291.7 | May 2013 | 26/6/13 | 1ወር |
| 7. | Nile petroleum | 12936.88 | Augest2012-may2013 | 21/6/13 | 19 ወር |
| 8. | koble Ethiopia ltd | 12954 | March-may2013 | 17/6/13 | 2ወር ከ17 ቀን |
| 9. | EPSE | 107000000 | April 2013 | 11/6/13 | 1ወር ከ17ቀን |
| 10. | Yetebaberut | 3587420 | Jan-march 2013 | 14/5/13 | 3ወር ከ4 ቀን |
| 11. | EPSE | 107000000 | March 2013 | 8/5/13 | 1ወር ከ14 ቀን |
| 12. | National oil Ethiopia | 191328.01 | Jan-march 2013 | 24/4/13 | 3ወር |
| 13. | Kobil Ethiopia | 8175.1 | Jan-feb2013 | 27/3/13 | 2ወር |
| 14. | EPSE | 107000000 | Feb 2013 | 29/3/13 | 1ወር |
| 15. | wegagen | 14025.52 | Jan 2013 | 11/3/13 | 1ወር ከ11 ቀን |
| 16. | Yetebaberute | 42017.7 | Oct & Dec 2013 | 8/3/13 | 5ወር ከ3ቀን |
| 17. | NOE | 129485.02 | April & may 2012 | 13/2/13 | 9ወር ከ13 ቀን |
| 18. | Commet transport | 106350 | July 2012- Nov 2012 | 22/1/13 | 5ወር |

**አባሪ 1.2፡ የ2006 በጀት አመት ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበገቢ**

| ተ/ቁ | ገቢ ሰብሳቢው ድርጅት | የገቢ መጠን | ገቢ የተሰበሰበበት ወራት | ባንክ ገቢ የሆነበት ቀን | የዘገየበት ወራት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Dallol oil s.c | 6,623.89 | April- julay/2014 | 1/9/2014 | 5 |
| 2 | wegagen bank s.c | 59,875.02 | Jun-14 | 21/9/2014 | 3 |
| 3 | Ethiopia petroliam supply enterprise | 107,000,000.00 | Jun-14 | 21/9/2014 | 2 |
| 4 | TAF oil plc | 7,342.00 | 14-Jun | 5/9/2014 | 2 |
| 5 | kobil Ethiopia plc | 2,773.40 | may-june | 29/7/2014 | 2 |
| 6 | Yetebaberut beherawi petroleum s.c | 59,409.60 | april-june/2014 | 21/7/2014 | 3 |
| 7 | TAF oil plc | 7,683.70 | April- may/2014 | 11/7/2014 | 3 |
| 8 | wegagen bank s.c | 57,261.02 | Dec-13 | 19/6/2014 | 6 |
| 9 | wegagen bank s.c | 40,650.39 | 14-Feb | 16/4/2014 | 2 |
| 10 | ethiopia petroliam supply enterprise | 107,000,000.00 | Mar-14 | 19/6/2014 | 3 |
| 11 | TAF oil plc | 7,780.30 | febrary-march/2014 | 13/5/2014 | 3 |
| 12 | Commet transport S.C | 445,356.44 | - | 4/12/2013 | - |
| 13 | Yetebaberut beherawi petroleum s.c | 32,776.70 | January- march/2014 | 14/5/2014 | 4 |
| 15 | TAF oil plc | 11,789.70 | November/13- jan/14 | 23/04/2014 | 5 |
| 17 | Commet transport S.C | 668,910.86 | - | 10/3/2014 | |
| 18 | Yetebaberut beherawi petroleum s.c | 36,163.20 | oct-13 - dec-13 | 24/2/2014 | 4 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 19 | wegagen bank s.c | 10,229.29 | Oct-14 - Nov-14 | 15/1/2014 | 3 |
| 20 | TAF oil plc | 14,787.80 | July-13 - Oct-13 | 9/1/2014 | 6 |
| 21 | National oil Ethiopia | 77,220.72 | 13-May | 13/12/2013 | 7 |
| 22 | TAF oil plc | 53,352.70 | March-12 - jun-13 | 23/9/2013 | 18 |
| 23 | Commet transport S.C | 398,834.00 | | 14/11/2013 | |
| 24 | kobil Ethiopia plc | 8,083.00 | aug-13 - oct-13 | 7/11/2013 | 4 |
| 25 | Yetebaberut beherawi petroleum s.c | 23,608.50 | Jul-13 - sep-13 | 6/11/2013 | 4 |
| 26 | Dallol oil s.c | 3,132.20 | Jan-12 - Jun-13 | 25/9/2013 | 21 |
| | | | | | |

**አባሪ 1.3 የ2007 በጀት አመት ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበገቢ**

| ተራቁጥር | ገቢ.የተሰበሰበበትድርጅት | የገቢ.መጠን | የመቹ ወር እንደገባ | ገቢ. የተሰበሰበበት ቀን | ሳይሰበሰብ የዘገየበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | Total Ethiopia | 88130.6 | May2015 | 30june2015 | 1ወር |
| 2. | Ethiopian petroleum supply enterprise(EPSE) | 107000000 | May2015 | 30june2015 | 1ወር |
| 3. | Nile petroleum | 970.3 | Dec31, 2014 | 25 june 2015 | 7ወር |
| 4. | Nile petroleum | 796.21 | June1,2013-dec 31,2013 | 25 june 2015 | 6ወር |
| 5. | Wegagen | 97832.54 | July 2014-may2015 | 17 june2015 | 10 ወር ከ17 ቀን |
| 6. | Wegagen | 102306.96 | Feb 2015 | 10june 2015 | 3 ወር ከ10 ቀን |
| 7. | TAF oil Ethiopia | 28720.4 | oct-march2015 | 27 may 2015 | 4ወር |
| 8. | Yetebaberut | 34838.2 | Jan-march 2015 | 12 may 2015 | 3ወር ከ12 ቀን |
| 9. | Dallol oil S.C | 3186.72 | Jan-march 2015 | May 8/2015 | 3ወር ከ8 ቀን |
| 10. | Wegagen | 193944.13 | April2015 | 27 april2015 | - |
| 11. | Wegagen | 171943.7 | ? | 30march2015 | - |
| 12. | Yetebaberut | 31574.7 | Dec 2014 | 09 march 2015 | 2ወር ከ9 ቀን |
| 13. | Comet transport | 1481510.45 | 5/9/2012- 2/8/2013 | 13 feb2015 | የአንድ አመቱን ከ18 ወር በኃላ |
| 14. | TAF oil Ethiopia | 10136.7 | Aug &sep 2014 | 04/mar 2015 | 7ወር |
| 15. | Yetebaberut | 23748.2 | July-sep2014 | Jan 26/2015 | 6ወር |
| 16. | Dallol oil | 24352.57 | July-dec 2014 | Jan 27/2015 | 6 ወር |
| 17. | TAF Oil Ethiopia | 1399 | july 2014 | 02/jan2015 | 5ወር |
| 18. | Yetebaberut | 23748.2 | July-sep 2014 | 29 dec 2014 | 5ወር |
| 19. | EPSE | 107000000 | July2014 | 7/oct/2014 | 2ወር ከ7ቀን |

**አባሪ 1.4 የ2008 በጀት አመት ፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበ ገቢ**

| ተ.ቁ | ገቢ ሰብሳቢው ድርጅት | የገቢ መጠን | ገቢ የተሰበሰበበት ወራት | ባንክ ገቢ የሆነበት ቀን | የዘገየበት ወራት |
|---|---|---:|---|---|---|
| 1 | wegagen bank s.c | 78,671.69 | Jan-16 - Feb-16 | 8/3/2016 | 2 |
| 2 | National oil Ethiopia | 187,231.14 | 15-Dec | 2/3/2016 | 2 |
| 3 | Dallol oil Plc | 1,455.60 | Nov-Dec/2016 | 25/1/2016 | 2 |
| 4 | TAF oil Plc | 6,368.80 | sep-oct/2016 | 14/12/2015 | 3 |
| 5 | kobil Ethiopia plc | 8,156.20 | sep-oct/2016 | 25/11/2015 | 2 |
| 6 | National oil Ethiopia | 89,661.15 | 15-Sep | 6/11/2015 | 2 |
| 7 | wegagen bank s.c | 774.18 | | 20/10/2015 | |
| 8 | TAF oil Plc | 14,873.30 | Jul-Aug/2015 | 2/10/2015 | 3 |
| 9 | Dallol oil Plc | 392.90 | Jul-Aug/2015 | 1/10/2015 | 3 |
| 10 | Commet transport S.C | 2,634,833.09 | | 18/9/2015 | |
| 11 | kobil Ethiopia plc | 6,187.60 | May-Jun/2015 | 24/8/2015 | 3 |
| 12 | Yetebaberut beherawi petroleum s.c | 53,274.96 | May-Jun/2015 | 7/8/2015 | 3 |
| 13 | National oil Ethiopia | 282,679.20 | May-Jun/2015 | 5/7/2015 | 2 |
| 14 | Ethiopia postal service | 30,952,780.00 | | 22/6/2016 | |
| 15 | kobil Ethiopia plc | 9,981.47 | Mar - Apri/2016 | 1/6/2016 | 3 |
| 16 | Commet transport S.C | 750,000.00 | | 19/4/2016 | |
| 17 | Ethiopia postal service | 15,886,485.00 | | 10/5/2016 | |
| 18 | Dallol oil Plc | 52.64 | 16-Feb | 10/5/2016 | 3 |
| 19 | TAF oil Plc | 3,097.30 | 16-Jan | 25/4/2016 | 3 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 20 | Yetebaberut beherawi petroleum s.c | 16,171.35 | Dec-15 - Feb-16 | 7/4/2016 | 4 |
| 21 | Ethiopia postal service | 14,815,155.00 | | 22/7/2008 | |
| 22 | Ethiopia postal service | 5,264,338.75 | | 24/2/2016 | |

አባሪ 1.5 የ2009 በጀት አመትፅ/ቤቱ ከነዳጅ ፣ ዘይትና ቅባት ታሪፍ እንዲሁም ድንበር አቋርጠው ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች የተሰበሰበ ገቢ

| ተራ ቁጥር | ገቢ የተሰበሰበበት ድርጅት | የገቢ መጠን | የመቼ ወር እንደገባ | ገቢ የተሰበሰበበት ቀን | ሳይሰበሰብ የዘገየበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | Yetebaberut | 33325.55 | Dec 2016-jan2017 | Feb2017 | 1ወር |
| 2. | TAF oil plc | 25386.96 | Dec 2016 | Feb2017 | 1ወር |
| 3. | Wegagen bank | 125380.07 | Jan 2017 | Feb2017 | - |
| 4. | Kobll | 4693.3 | Dec 2016 | Feb2017 | 1ወር |
| 5. | Ethiopian petroleum supply enterprise (EPSE) | 196573766.42 | Dec2016 | 4feb2017 | 1ወር4ቀን |
| 6. | TAF oil Ethiopia | 7970.1 | Oct 2016 | 20dec2016 | 1ወር ከ20ቀን |
| 7. | Yetebaberut | 31366.02 | Oct & nov 2016 | 16dec2016 | 1ወር ከ16 ቀን |
| 8. | Oil Libya | 57505.5 | Sep 2016 | 3dec2016 | 2ወር |
| 9. | TAF oil plc | 6646.9 | Sep2016 | 23nov2016 | 2ወር ከ23 ቀን |
| 10. | Oil Libya | 70332.6 | Aug2016 | Oct2016 | 1ወር ከ16 ቀን |
| 11. | Libya oil Ethiopia | 61444.5 | July2016 | Oct 2016 | 2ወር ከ16 ቀን |
| 12. | TAF oil plc | 4657 | Aug 2016 | Oct2016 | 1ወር ከ16 ቀን |
| 13. | Koble Ethiopia | 6346.6 | July2016 | Oct 2016 | 2ወር ከ16 ቀን |
| 14. | National oil Ethiopia | 13059766 | Aug2016 | 30sep2016 | 1ወር |
| 15. | TAF oil Ethiopia | 2060.1 | July2016 | 26sep2016 | 2 ወር |
| 16. | National oil Ethiopia | 68288.74 | July2016 | 5sep2016 | 1 ወር |
| 17. | wegagen bank | 10040.45 | July2016 | Sep72016 | 2ወር |
| 18. | TAF oil Ethiopia | 4659.4 | June2016 | Aug16/2016 | 1ወር ከ15ቀን |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 19. | Kobil oil Ethiopia | 7051 | May&june2016 | Aug 10/2016 | 2ወር ከ10 ቀን |
| 20. | Yetebaberut | 41349.86 | June2016 | Aug10/2016 | 1ወር ከ10 ቀን |
| 21. | Libya oil Ethiopia | 79330.30 | June2016 | Aug12/2016 | 1ወር ከ12 ቀን |
| 22. | National oil Ethiopia | 172444.13 | April2016 | Aug2/2016 | 3ወር ከ2ቀን |
| 23. | TAF oil ethiopia | 6943.2 | May2016 | Aug1/2016 | 2ወር |

## አባሪ 2፡ ለመንገድ ኤጀንሲዎች 20 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፍያ እንዲጠቀሙ የተፈቀደበት ጊዜ

| ተ/ቁ | የመንገድ ኤጀንሲው ስም | በጀት አመት | መፈቀድ የነበረበት | ክፍያው የተፈቀደው | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አማራ ገጠር መንገድ ባለስልጣን | የ2008 | በ1/11/2007 | በ20/03/2008 | 4ወር ከ20 ቀን |
| 2. | ለጎንደር ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን | የ2009 | በ1/11/2008 | በ23/02/2009 | 3ወር ከ23 ቀን |
| 3. | ለጎንደር ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2007 | በ30/02/2008 | 4ወር |
| 4. | ባህርዳር ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን | የ2009 | በ1/11/2008 | በ04/02/2009 | 3ወር ከ4 ቀን |
| 5. | ለባህርዳር ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2007 | በ08/06/2008 | 7ወር ከ8ቀን |
| 6. | ደብረ ማርቆስ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2006 | በ26/09/2007 | 10ወር ከ26ቀን |
| 7. | ደብረ ማርቆስ ማዘጋጃ ቤት | የ2009 | በ1/11/2008 | በ17/06/2009 | 7ወር ከ17 ቀን |
| 8. | ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን | የ2008 | በ1/11/2006 | በ19/02/2007 | 3ወር ከ19 ቀን |
| 9. | ኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን | የ2009 | በ1/11/2008 | በ10/02/2009 | 3ወር ከ10 ቀን |
| 10. | ጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2007 | በ03/03/2008 | 4ወር ከ3 ቀን |
| 11. | ጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2009 | በ1/11/2008 | በ23/02/2009 | 3ወር ከ23ቀን |
| 12. | ወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2007 | በ1/04/2008 | 5ወር |
| 13. | ወሊሶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2009 | በ1/11/2008 | በ23/03/2009 | 4ወር ከ23 ቀን |
| 14. | የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን | የ2008 | በ1/11/2007 | በ20/03/2008 | 4 ወር ከ20 ቀን |
| 15. | የደቡብ መንገዶች ባለስልጣን | የ2009 | በ1/11/2008 | በ10/02/2009 | 3 ወር ከ10 ቀን |
| 16. | ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2007 | በ14/04/2008 | 5ወር ከ14 ቀን |
| 17. | ወልቂጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2009 | በ1/11/2008 | በ17/06/2009 | 7ወር ከ17 ቀን |
| 18. | ሃዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2008 | በ1/11/2007 | በ03/03/2008 | 4ወር ከ3 ቀን |
| 19. | ሃዋሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | የ2009 | በ1/11/2008 | በ4/02/2009 | 3ወር ከ4 ቀን |